# የቦታው ስም ቀራንዮ ነው።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላዩ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት

በሊቃውንት ጉባኤ ታይቶና ተመርምሮ፤ በሕዝብ ግንኙነት መምሪያ የተዘጋጀ


**ዋና አዘጋጅ**

መጋቤ ሰላም ቀሲስ ሰሎሞን ቶልቻ

**ም/አዘጋጅ**

መጋቤ ሃይማኖት ጌታባለው አድማሱ

**ኮምፒዩተር ጽሑፍና ዝግጅት**

ሳዕከ ሰላም ነቢዩ ኤልያስ

**ግራፊክስ ዲዛይን**

ተመስገን ቶማስ

**ትርጉም**

መ/ሰ ቆሞስ አባ ቃለጽድቅ ሙሉጌታ (ዶ/ር)

መምህር አካለወልድ ተሰማ (ዶ/ር)

መምህር ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል

**ፎቶግራፍ**

መልአከ ሰላም አባ ኪሮስ ወልደአብ

**ኅትመት**

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት


## ማውጫ


የመጽሔቱ መልእክት ........................................... 02

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ አባታዊ መልእክት ............. 04

የብፁዕ ጠቅላዩ ሥራ አስኪያጅ መልእክት ...................... 07

የብፁዕ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊ መልእክት .................. 10

የመንፈሳዊ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ መልእክት .......... 12

የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ መልእክት .... 14

መስቀል ኀይላችን ነው ........................................... 16

መስቀል በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ..... 22

የቦታው ስም ቀራንዮ ነው! ....................................... 26

የመስቀል በዓል አከባበር ታሪክ በኢትዮጵያ .................. 36

ነገረ መስቀል ከመንበረ ጸባዖት እስከ ቀራንዮ ................ 40



© መስከረም ፲፮ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም



አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ

“የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”

## የመጽሔቱ መልእክት

# የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው ምን ሠሩ?

የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው ቅዱሳን ሐዋርያት ኋላም በአግረ ሐዋርያት የተተኩ ቅዱሳን ሁሉ የመስቀሉ ፍቅር ሲገባቸው ምን ሠሩ? እኛንስ የመስቀሉ ፍቅር እንዴት ይግባን?

“ዘኢያጥብዐ ወዘኢነሥአ መስቀለ ሞቱ ወዘኢተለወኒ ድኅሬየ ኢይደሉ ሊተ ወኢይክል ይፀመደኒ” “መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም” (ማቴ.10:38)

የዚህ ኃይለ ቃል ጥሪ አገልጋይ ለሆነ ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ለዳነ ሁሉ መስቀሉን መሸከም ይጠበቅበታል። እያንዳንዱ አገልጋይ ሆነ ምእመን ዕለተ ዐርብን እያሰበ ሊሸከመው የሚገባው መስቀል አለው። መስቀሉን መሸከማችንን በዕለት የኑሮ ሕይወት ልናየው ይገባል። ይህም የመስቀሉን ፍቅር በማሰብ በኑሮ በመተርጎም ነው። የክርስቶስ መከራ መስቀሉ በራስ ቀላችን ውስጥ እንደተሰቀለ ልንቆጥረው ይገባል። ጌታ የተሰቀለበት ጎልጎታ የራስ ቅል ሥፍራ ነውና። የራስ ቅል ሥፍራ ሲባል የመስቀሉ መከራ የክርስቶስ ፍቅር በራስቅላችን ውስጥ ተስሎ እንዲኖር ነው።

እርሱ የተሰቀለው እኛን ከወደቅንበት ሊያነሳን ለቤዛነት ነው። የመስቀሉ ምሥጢር ፍፁም ቤዛነት ነው። ሰው ከወደቀበት ለመነሳት /ተዘክሮተ መስቀል/ መስቀሉን ማሰብ በዓይነ ሕሊና ተስሎ ማየት ይገባዋል። የማስተዋል ጸጋቸው ተገፍፎ አዚም የጋረዳቸው የገላትያ ሰዎች በዓይነ ሕሊናቸው ፊት ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተስሎ በአለማየታቸው ተገስጸዋል። ገላ 3÷1 እኛም የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን ከመለየየት ከአዚም ግርዶሽ ተላቀን ዘወትር ክርስቶስ ስለ እኛ በሕሊናችን ተሰቅሎ ፍቅሩ በልባችን ተስሎ እናየዋለን። የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው መስቀሉን ይሸከማሉ፤

መስቀልን መሸከም! የመስቀሉ ፍቅር ስንል ለሰው ልጆች ቤዛነት ዋጋ የተከፈለበትን የክርስቶስን መከራ ማሰብ ነው። ስለመስቀሉ ፍቅር ስናነሳ የመስቀሉን መከራ እንሸከማለን። ዛሬ የመስቀሉ መከራ የተባሉት እንደጥንቱ በመጋዝ መሰንጠቅ፣ በሰይፍ መታረድ፣ በእሳት መቃጠል ብቻም አይደለም። ዛሬ የመስቀል መከራዎች ወይም ፈተናዎች ክርስቶስ ድል የነሳቸው ናቸው። እነዚህም፡- ዝሙት፣ ርኩሰት፣ ጣኦት ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅናት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ መለያየት በአጠቃላይ ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች እንደጻፈው የሥጋ ፍሬን ድል መንሳት የዚህ ዘመን መስቀላችን ነው። የመስቀሉ ፍቅር ሲያድርብን የሥጋ ፍሬዎችን ድል በማድረግ በመስቀሉ ኃይል የመንፈስ ፍሬዎች እናፈራለን። እነሱም፡ - ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋህነት፣ ራስን መግዛት፣ መተሳሰብ ናቸው።

የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን በዋንኛነት ጌታ የተናገራቸው የወርቃማው ሕግ ፈጻሚዎች እንሆናለን። ወርቃማው ሕግ ምንድን ነው ? ‹‹በአንተ ላይ ሊደረግብህ የማትፈልገውን ነገር በሌላው ላይ አታድርግ›› (ማቴ.7:12) የመስቀሉ ፍቅር የገባው ለዚህ ቃል ተገዥ ነው፡ ፡ የሃይማኖት መሠረትም ሰውን መውደድ ነው። ሰው ወንድሙን ከወደደ አይሰርቅም፣ አይዋሽም፣ አይገድልም፣ አያመነዝርም። ምክንያቱም ወንድሙን ይወዳልና በእርሱ ላይ እነዚህ እንዲደረግበት ስለማይፈልግ በሌላውም ላይ አያደርገውም። የወርቃማው ሕግ ተገዥ የምንሆነው የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን ነው። በመስቀሉ ዘለዓለማዊ ፍቅር ተገልጾበታል።

በአጠቃላይ ዛሬ በሀገራችንና በመላው ዓለም የመስቀልን በዓል ስናከብር የመስቀሉን ፍቅር ተረድተን ሊሆን ይገባል። ታዲያ መስቀል አምሮ፣ ደምቆ፣ አብቦና ፈክቶ በሚከበርበት ታላቅ ሀገር ስደት፣ መገዳደልና እፈና፣ ጠብ፣ ክርክር፣መፈናቀል፣ ሰላም ማጣት ወዘተ በዝቶና ሰላም የሰማይ ያክል ርቆን በዓለ መስቀልን ስናከብር የመስቀሉ ፍቅር ገብቶናል ወይ? ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል?

የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን ክርስቶስ በሕሊናችን ተሰቅሎ እናየዋለን። (ገላ 3÷1) የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን የሥጋ ፍሬን አሸንፈን የመንፈስ ፍሬን እናሳድጋለን። (ገላ 5÷22)

የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው ክርስቶስን ያዩታል ቅዱስ እስጢፋኖስ በድንጋይ ሲወገር ሰማይ ተከፍቶ ክርስቶስን አየው። የመስቀሉ ፍቅር በድንጋይ አስወግሮ የክርስቶስን ፊት ያሳያል ፣የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን የድኅነት ዓላማ (መጨበጫን) እንይዛለን፣ ገነትን መንግሥተ ሰማያትን በተስፋ እናያለን፣ ትክክለኛውን የመዳን መንገድ እንይዛለን፣ ይህ ብቻም አይደለም የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን ክርስቶስን ለማግኘት እንናፍቃለን። ልሄድ ከአንተ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ (ፊል.1:20-23) በእውነትም ደስ ብሎን በሞት መንገድ ወደ ክርስቶስ እንኄዳለን።

በአጠቃላይ የመስቀል ትርጉምና የመስቀሉ ፍቅር ካልገባን መስቀልና ማክበራችን ብቻ በቂ አይደለም፤ ገብቶን ልናከብር ይገባል። በዓለ መስቀል ዛሬ እንደ ሀገርም፣ እንደ ቤተክርስቲያንም፣ እንደ ዓለምም በምድራችን ላለው ፈተና ሁሉ ገብቶን ከአከበርነው ብቸኛው መፍትሔና መልስ ሰጪ በዓል ነው።

ይህ የ2018 ዓ.ም የበዓለ መስቀል መጽሔት ቤተክርስቲያና በአሏት ሊቃውንት ተጽፎ በሊቃውንት ጉባኤ ታይቶና ተመርምሮ የተዘጋጀ ልዩ መልዕክትና ትምህርት ያለው መጽሔት ነው። መጽሔቱ ከወረቀት ኅትመት በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያና የዲጂታል ሚዲያዎች ስለተቀመጠ እንድታነቡት በእግዚአብሔር ፍቅር ማሳሰብ እንወዳለን። በዓሉን የመስቀሉ ፍቅር ገብቶን እንድናከብረው አምላካችን ይርዳን።

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕዝብ ግንኙነት መምሪያ**

## “የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”





# የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ
# አባታዊ መልእክት

‹‹ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ወለጽልአ ቀተሉ ቦቱ፤ በመስቀሉ ሰላምን አደረገ ጥልንም በሱ ገደለው››

(ኤፌ. ፪÷፲፫፡፲፮)

ክርስቶስ ከመሰቀሉ በፊት በደል የወለደው ጥል በእግዚአብሔርና በምድር ላይ በሚኖሩ ፍጡራን፥ በተለይም በእግዚአብሔርና የበደሉ ምክንያት በሆነው የሰው ልጅ መካከል ጥል ሰፍኖ ነበር፤ ጥሉ እግዚአብሔርንና ሰውን ሰማያውያንና ምድራውያንን በሙሉ የለያየ ነበር፡፡ እግዚአብሔርና ሰው ተለያዩ ማለት፥ ሰው ከእግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ከሆነው ክብርና ሕይወት ተለየ ማለት ነው፡፡ ትልቁ ቅጣትና አደገኛው ሞትም ይህ ነው፡፡

አዳምና ልጆቹ የበደል ቅጣት ተሸካሚዎች በመሆናቸው በዚህ ዓለም የሚደርስባቸው ሞተ ሥጋ ሳይበቃ በነፍሳቸውም የእግዚአብሔር ወደ ሆነው ገነተ ተድላ ሳይሆን ወደ መካነ ኵነኔ ማለትም ወደ ቅጣት ስፍራ ይወረወሩ ነበር፡፡ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር የተለየ ፍጡር የእግዚአብሔር ወደ ሆነው ገነተ ተድላ መግባት አይችልምና ነው፡፡ ይህንንም እውነት በቅዱስ ወንጌል ተጽፎ የሚገኘው የባለጸጋውና የደሃው ሰፊር ልዩነት ያስረዳናል፡፡ (ሉቃ. ፲፮፥፲፱-፴፩)

የሰው ልጅ በዚህ ሁኔታ ከእግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ከሆነው ነገር ተለይቶ ለአምስት ሺሕ አምስት መቶ ዘመናት ያህል ኖሮአል፡፡ ክብርና የክብር ክብር ይድረሰውና፥ እግዚአብሔር አምላካችን በዚህ ረጅም ዘመን ሰውን ያለ ተስፋ አልተወውም፤ ይልቁኑም የተስፋ ቃሉን በነቢያት በኩል በየዘመኑ እየገለጸ ሰውን ያጽናናው ነበር፤ የተስፋው ጭብጥ ይዘትም እግዚአብሔር ሰውን በመሲሑ ቤዛዊ ደም እንደሚያድነው የሚያመለክት ነበር፡፡

እግዚአብሔር ዓለምን የሚያድንበት ዘመን ሲደርስ አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ላከው፡፡ እርሱም ከሥጋችን ሥጋ ከነፍሳችን ነፍስ ነሥቶ ሰው ሆነ፤ በዚህ ዓለም ተገለጠ፡፡ ይህም ማለት ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ ማለት ነው፡፡

በዚህ ተዋሕዶ የተወለደ ወልደ እግዚአብሔር ወልደ ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅን በቤዛዊ ሞቱ ሊያድን በዚህ ዓለም እየተመላለሰ ነገረ ድኅነተ ሰብእን አስተማረ፡፡ የእግዚአብሔርነትንና የሰውነትን ሥራ ባለመለያየት፥ ባለመጠፋፋት፥ ባለመቀላቀልና ባለመለዋወጥ አንድ ሆኖ ሠራ፡፡ በሌላ አባባል፥ በተዋሕዶው ለፍጡራን የማይቻሉ ተአምራትን በማድረግ እግዚአብሔርም ሰውም እንደሆነ አሳየ፤ የእግዚአብሔር መንግሥትና የድኅነት መንገድ ምን እንደሆነ ለሰው ልጆች በምልአት አስተማረ፡፡

በመጨረሻም ስለ ዓለም ድኅነት ሲል በዕፀ መስቀል ተሰቅሎና ቤዛዊ ደሙን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ በበደላችን ከመጣብን የሞት ቅጣት አዳነን፡፡ በፈሰሰው ደሙ ቅጣታችንን በእኛ ፋንታ ተቀብሎ በሞተበት ቅፅበት የሞት ቅጣት የዕዳ ደብዳቤያችን ተቀደደ፤ ገነተ ተድላም ተከፈተ፤ ወደዚያ እንድንገባም ተፈቀደ፡፡ ‹‹ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ›› የሚለውን ታላቅ የምሥራች በመስቀሉ ላይ ሆኖ ለሁላችን አበሠረን፡፡ በመሆኑም በፈሰሰው ደሙ ለዋጀን ወይም ለገዛን ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ምስጋና ይሁንና፤ ዛሬ እንደ ብልሁ ወንበዴ ‹‹ጌታ ሆይ፥ በመንግሥትህ ስትመጣ አስበን›› እያልን በእምነት ለምንጸልይ ሰዎች የሚጠብቀን መካነ ኵነኔ ሳይሆን መካነ ዕረፍት ነው፡፡

እኛ ክርስቲያኖች በዓለ መስቀልን እጅግ በደመቀ ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዐት የምናከብረው ከመካነ ኵነኔ አውጥቶ ወደ ቀደመው ርስታችን ወደ ገነተ ተድላ የመለሰን ስለሆነ ነው፡፡ ለዚህም ነው ‹‹መስቀል መልዕልተ ኵሉ ነገር -- መስቀል ከሁሉም ነገር በላይ ነው›› በማለት አባታችን ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ዘምሮ የሚያዘምረን፡፡ ቅዱስ መስቀልን ስናስብ በዋናነት ክርስቶስን፥ የክርስቶስን ፍቅርና ነገረ አድኅኖቱን እናስታውሳለን፡፡ ቅዱስ መስቀሉን የምንሳለመውና የምናከብረውም በትእምርተ መስቀሉ ውስጥ በምሥጢረ እምነት ላለው መድኅኔ ዓለም ክርስቶስ ነው፡፡

የአንድን ሀገር ሰንደቅ ዓላማ ማክበር ማለት የሀገሩን ሕዝብ ማክበር ማለት እንደሆነ ሁሉ፤ ትእምርተ መስቀሉን ማክበር ማለት ክርስቶስን ማክበርና መሳለም ማለት እንደሆነ ሊሠመርበት የሚገባ ሐቅና እውነት ነው፡፡ የቅዱስ መስቀልን ነገር ጠለቅ አድርገን ስናስተውለው ውስጠ ምሥጢሩ ይቅርታን፥ ዕርቅን፥ መዳንን፥ ሰላምን፥ አንድነትን፥ አብሮነትንና በደል መተውን ፍንትው አድርጎ ያሳየናል፡፡

ቅዱስ መስቀልን ማክበራችን፥ መውደዳችንና መሳለማችን ተገቢ ነው፡፡ ይሁንና መውደድ ብቻ ሳይሆን፥ በራሱ የቅዱስ መስቀልን በረከት በምልአት እንድናገኝ መውደዳችን በተግባር መገለጽ መቻል አለበት፡፡ ለቅዱስ መስቀል የምናደርገው ፍቅርና ክብር በቀጥታ ለእግዚአብሔር የሚደረግ ፍቅር እንደሆነ ልብ ብለን እናስተውል፡፡ ለእግዚአብሔር የሚደረግ ፍቅር ደግሞ በሙሉ ነፍሳችን፥ በሙሉ ልባችን፥ በሙሉ

ዕውቀታችንና በሙሉ ኀይላችን መደረግ እንዳለበት ራሱ ባለቤቱ ነግሮናል። እውነቱ ይሄ ከሆነ መስቀሉን ስንወድ የመስቀሉን መልእክት በሥራ ለመተርጐም በቁርጠኝነት በመነሣት መሆን አለበት። በቅዱስ መጽሐፍም በተግባርም እንደተገነዘብነው የመስቀሉ መልእክት በደልን እርግፍ አድርጋችሁ ተዉና ታረቁ፤ ይቅርም ተባባሉ፤ በመካከላችሁ ፍጹም ሰላም ይስፈን፤ አንድ ሁኑ እንጂ አትለያዩ፤ ተባበሩ እንጂ አትጨካከኑ፤ የሰው ወገንን ሁሉ እንደራሳችሁ አድርጋችሁ ውደዱ የሚል ነው።

ታዲያ ይሄ ሁሉ የታለ? ፍጹም ሰላምን የሚያጐናጽፈን ይህ መልእክተ መስቀል እኛን ፈጽሞ የማይመለከት እስኪመስል ድረስ ተዘንግቷል። እኛ እየኖርን ያለነው እንደ ነገረ መስቀሉ ሳይሆን በተቃራኒው ነው። ክርስቶስ በመስቀሉ የጥል ግድግዳን ቢንድልንም፥ ብዙዎች 'ጥሉ ይሻለናል' ብለው በመነሣት፦ ግጭትን፥ መለያየትን፥ መጨካከንን፥ መገዳደልን፥ ዝርፊያን፥ እገታን፥ መድፈርን በዘመቻ መልክ ዳር እስከ ዳር እየተገበሩት ይገኛሉ። ይህ በዘመናችን እየሆነ ያለ እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ይህ ዓይነቱ ምርጫ ሊጎዳንና ሊያጠፋን ካልሆነ በቀር በምንም ተኣምር ሊጠቅመን አይችልም፤ በጠብ የተጠቀመ ሰውም ሆነ ሀገር በምንም ዐይነት አናገኝም።

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የመንፈስ ቅዱስ ልጆቼ ሆይ! እባካችሁ ወደ ዕርቅና ሰላም፥ ወደ ስምምነትና አንድነት እንምጣ፤ ልማታችንና ዕድገታችን፥ ክብራችንና ግርማችን፥ ኀይላችንና ሞገሳችን ያለው በይቅርታና በዕርቅ ውስጥ ነውና። ይህንን ለማድረግ ደግሞ በልበ ሰፊነትና በቅንነት ከመወያየት ያለፈ የሚያስከትልብን ጉዳትም ሆነ ኪሳራ የለም። ሁላችሁም ልጆቻችን በያላችሁበት ቆም በሉና አስቡ፤ ስለ ራሳችሁና ስለ መጭው ትውልድ ዘላቂ ጥቅም አርቃችሁ ተመልከቱ። እኛም ሆን መጪው ትውልድ ተጠቃሚ መሆን የምንችለው አንዲት ኢትዮጵያን እንደ ብዙ፥ ብዙዋን ኢትዮጵያ እንደ አንዲት አድርገን ስንከባከባት ነው።

ይህንንም እውነት የምናረጋግጠው በሰላማዊ ውይይትና በመደማመጥ፥ አከራካሪ ለሆኑ ነገሮችም ጊዜ በመስጠትና ሰከን ብሎ በማሰብ፥ ጥያቄዎችን ሁሉ በውይይትና በሕግ ብቻ ለመመለስ ቁርጠኛ በመሆን፥ እንዲሁም ለውይይት ዕድል በመስጠት እንጂ በኀይልና በጦርነት አይደለም። ፍትሕና ርትዕን ማስፈን አለብን፤ የሰው ልጆችን በሕይወት የመኖር ሕገ ፈጣሪን ማክበር አለብን፤ እኩልነትና አንድነት ማረጋገጥ አለብን፤ ይህንን ለማሳካት ፈሪሀ እግዚአብሔርን የጋራ ዳኛ አድርገን መቀበል አለብን። ይህንን ስናደርግ የነገረ መስቀል መልእክት በሕዝባችንና በሀገራችን በተግባር ይተረጐማል።

በመሆኑም ይህ የጀመርነው አዲስ ዓመት እንደ መስቀሉ መልእክት ጥልን በዕርቅ ገድለን የሕዝባችንንና የሀገራችንን ሰላምና አንድነት እውን እናድርግ። ለዚህም በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም ዙሪያ ያላችሁ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሁሉ በጸሎት፥ በዕውቀት፥ በጎ ሐሳብና ምክርንም በመለገስ ያላሰለሰ ጥረት እንድናደርግ በእግዚአብሔር ስም አባታዊ መልእክታችንን እናስተላልፋለን።

እግዚአብሔር አምላክ የተባረከና የተቀደሰ በዓለ መስቀል ያድርግልን!

አምላካችን እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ! ይቀድስ!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፤ አሜን።

# አባ ማትያስ ቀዳማዊ

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአኲስም
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

መስከረም ፲፮ ቀን ፳፻፲፰ ዓ.ም

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ



# የብፁዕ ጠቅላዩ ዋና ሥራ አስኪያጅ መልእክት

“ወአነኒ እምከመ ተለዐልኩ እምድር እስሕብ ኵሎ ኀቤየ፤ እኔም ከምድር ከፍ ከፍ በአልኩ ጊዜ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ።”

(ዮሐ. 12÷32)

ጌታችን አምላካችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የድንግል ማርያምን ሥጋ ተዋሕዶ በፍጹም አምላክነትና ሰውነት ወደዚህ ዓለም የመጣው ትእዛዘ እግዚአብሔርን ተላልፎ በኀጢአት የወደቀውን የሰውን ዘር ለማዳን ነው፡፡ ሰው የበደለውና የወደቀው ደግሞ አትብላ የተባለውን ዕፀ በለስን በመብላቱ ነው፡፡ “እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና” (ዘፍ. 2÷16፡17)፡፡ ይህን ቃል

ባለመጠበቅና ባለመታዘዝ ኀጢአት ወደ ዓለም ገባ፣ በኃጢአትም ሞት። (ሮሜ 8÷3:4)

በሞት ጥላ ሥር የነበረ አዳምንና ልጆቹን ለማዳን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በዕፀ በለስ የመጣ በደልን በዕፀ መስቀል ሊያጠፋው በመስቀል ላይ ተሰቀለ። ቅዱስ ኤፍሬም ይህን ታላቅ ምሥጢር ሲያስረዳ፦

"ትምክህተ ኵልነ ድንግል ማርያም ዘበእንቲአሃ ተስዕረ ዘቀዳሚ መርገም እንተ ኀደረት ዲበ ዘመድነ በዕልወት ዘገብረት ብእሲት በልዐት እምዕፅ። በእንተ ሔዋን ተዐፅወ ኆኅተ ገነት ወበእንተ ማርያም ድንግል ተርኅወ ለነ ዳግመ። ከፈለነ ንብላዕ እምዕፀ ሕይወት ዘውእቱ ሥጋሁ ለክርስቶስ ወደሙ ክቡር፣ በእንተ ፍቅረ ዚአነ መጽአ ወአድኀነነ፤ ሔዋን ዕፀ በለስን በልታ ባደረገችው ዐመፅ በባሕርያችን ያደረ የቀድሞው እርግማን በእርሷ የጠፋልን አምላክን የወለደች ድንግል ማርያም የሁላችን መመኪያ ናት። ስለ ሔዋን የገነት ደጅ ተዘጋ። ዳግመኛ ስለ ድንግል ማርያም ተከፈተልን። ከዕፀ ሕይወት እንበላ ዘንድ አደለን። ይኸውም እኛን ስለመውደድ መጥቶ ያዳነን የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋው ክቡር ደሙ ነው" አለ። (ውዳሴ ማርያም ዘሐሙስ)

ድንግል ማርያም አለመታዘዝን በመታዘዝ አሸንፋ መመኪያችን ሆነች። ንጹሕ ሥጋንና ንጽሕት ነፍስን ይዛ በመገኘቷ አምላክ ለእናትነት መረጣት። ከእርሷ በነሣው ሥጋ፣ ዓለምን በመስቀል ተሰቅሎ ሲያድን እርሷ የድኅነታችን ምክንያት ሆነች። ጌታችን ይህን የመስቀል ሞቱን አስቀድሞ ሲናገር ነው "እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ባልኩ ጊዜ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ" ያለው። በዚህ ቃል ውስጥ ያለው ምሥጢር ጌታችን ስለእኛ በመስቀል ተሰቅሎ የሚሞት መሆኑን አስቀድሞ የሚናገር መሆኑ ነው። ቅዱስ መስቀል በቀራንዮ ከሰማይ ዝቅ ከምድር ከፍ ብሎ ተተክሎአልና። በቀደመ በደሉ ከእግዚአብሔር ርቆ የነበረ ሁሉ በዚህ መስቀል ምክንያት ተስቦ ወደ ራሱ ወደ ክርስቶስ የሚቀርብ መሆኑን የተናገረበት ደግሞ ሌላው ምሥጢር ነው። "ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው" እንዳለ ሐዋርያው። በኃጢአት ምክንያት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ጥል ነበረ። ይህን ሰው ከእግዚአብሔርና ሰው ከሰው ተጣልቶ የነበረበትን ጥል ክርስቶስ በመስቀሉ ገደለው። ሰውን ከራሱ ጋር አስታረቀ፣ ሕዝብና አሕዛብንም አንድ አደረገ።

ቅዱስ መስቀል እግዚአብሔር ዓለምን የታረቀበት፣ ለዘለዓለም ሕይወት የሚሆን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የሰጠበት ክርስቶስ የሚታይበት የመዳን ምሥጢር ነው። በዚህ ምክንያት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መስቀልን እጅግ ከፍ ከፍ አድርጋ ታከብረዋለች። ለዕፀ መስቀልኒ ከመ ተናገርነ ቅድመ እስመ በላዕሌሁ አንጠብጠበ ደመ ቃል ኢሐማሚ በባሕርየ ሥጋ ዘሐመ እንዲል፣ በላዩ የፈሰሰውን የክርስቶስ ደም ምክንያት በማድረግ ትሰግድለታለች። ይህን በመስቀሉ የተደረገልንን በማሰብ ክርስቶስን የምናመሰግነበት መሆኑን ቅዱስ ያሬድ ሲያመሠጥር፦ "በመስቀልከ ክርስቶስ ረዳእከነ፣ በመስቀልከ እሞት ባላሕከነ፣ ሕይወተ ጸጎከነ፣ ወወሃብከነ እምጽልመት ብርሃነ፤ ክርስቶስ ሆይ። በመስቀልህ ረዳኸን፣ በመስቀልህ ከሞት አዳንከን፣ ሕይወትን ሰጠኸን፣ ከጨለማ የምንወጣበት ብርሃንንም ሰጠኸን" ብሏል። ይህም ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔር ምእላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና በማለት ካስተማረው ጋር የተስማማ ነው (ቈላስ. 1÷19:20)።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመስቀልን በዓል ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በልዩ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዐት ታከብረዋለች። በበዓሉ የሚከናወኑ ሥርዓቶች ከሚያስተላልፉት ነገረ መለኮታዊ መልእክት በተጨማሪ የበዓሉን ታሪካዊ መሠረትም ይጠቁማሉ። በበዓሉ ዋዜማ የሚከናወነው የደመራው ሥነ ሥርዐት በዕሌኒ ንግሥት አማካይነት መስቀሉ በብዙ ጥረት ተፈልጎ የተገኘበትን መንገድ ይጠቁማል። ንግሥት ዕሌኒ መስቀሉ የተቀበረበትን ትክክለኛ ቦታ ለማግኘት ደመራ አስደምራ፣ በደመራው ጢስ እየተመራች መስቀሉን ለማግኘት በቅታለች። ዘርፈ ብዙ ትርጉም ያለው ይህ ኩነት ደመራ በመደመርና የመስቀሉን መገኘት በሚያበሥሩ የተለያዩ መንፈሳዊና ባህላዊ ሥነ ሥርዓቶች ይዘከራል።

የመስቀል በዓል በርካታ ተጨማሪ ፋይዳዎች ያሉት በዓል ነው። በክረምቱ ወራት በሚኖረው አስቸጋሪ የዓየር ጠባይ፣ በወንዞች ሙላትና በመንገዶች

አስቸጋሪነት ተራርቆ የነበረ ሕዝብ በአንድ አካባቢ ተሰባስቦ በዓሉን ያከብራል። ይህም ለሰዎች ሰላማዊ ግንኙነትና በበዓሉ ሰበብ ለሚፈጠረው መተባበርም ምክንያት ሆኖ ያገለግላል። ዛሬ ሁኔታዎች በእጅጉ ተቀያይረዋል። የመንገዶች ሁኔታና የግንኙነት መስመሮች የተሻሻሉ ቢሆንም የሰው ለሰው ግንኙነት ግን በተለያዩ ተጽዕኖዎች ምክንያት ቀንሷል። ምዕራባዊ ባህሎች ሀገራዊውን ባህል እየተጫኑ ነው። በዚህ መሰል ጊዜያት ላይ ሃይማኖታዊ አስተምህሮንና መንፈሳዊ ተግባራትን የሚጎዱ ነገሮችን በጥንቃቄ በማየት ሃይማኖታዊ ትውፊትን አጽንቶ መያዝ ያስፈልጋል። መስቀል ሰላም የተበሠረበት፣ ዕርቅ የተፈጸመበትና ድኅነት የተገኘበት እንደመሆኑ መጠንም ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች በዓሉን የሰላም መሠረትን በማጽናትና የሰላም ምሳሌ በመሆን ልናከብረው ይገባል።

ሰላም ጌታችን በቅዱስ መስቀሉ ያደረገልን ታላቅ ነገር ነው። ጥልን ማስወገድ ዕርቅ ያወርዳል፣ ሰላምንም ያስፍናል። እኔም ከምድር ከፍ ከፍ በአልኩ ጊዜ ሁሉን ወደእኔ እስባለሁ የሚለው የመድኀኒታችን ቃል በመስቀል በተደረገልን ታላቅ ነገር ወደእርሱ ኅብረት የተጠራን መሆኑን ይነግረናል። "ዐቃቢነ ዘኢይማስን መዝገበ ጽልመት እንተ ብነ በሥምረተ አቡከ አብራህከ ለነ ዘአውጻእከነ እማዕምቅ ውስተ ብርሃን ወወሀብከነ ሕይወተ እሞት ወጸጎከነ እምግብርናት ግዕዛነ ዘበመስቀልከ አቅረብከነ ኀበ አቡከ መልዕልተ ሰማያት በወንጌል መራሕከነ -- የማይለወጥ ጠባቂያችን በእኛ የነበረውን ጨለማ በአባትህ ፈቃድ አራቅህልን፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን አወጣኸን ከሞት አድነህ ሕይወትን ሰጠኸን ከመገዛት ነጻ አወጣኸን፣ በመስቀል በሰማይ ወዳለው ወደ አባትህ ያቀረብከን አቤቱ በወንጌል መራኸን" እያልን የምናመሰግነው ርቀን የነበርን ወደራሱ ስቦ ያቀረበን መሆኑን አምነን ነው። ስለዚህ ወደእርሱ የቀረብን ሁላችን ሰላምን የምንፈልግና ስለሰላም የምንኖር ልንሆን ይገባል።

የቅዱስ መስቀል በዓል ያለፈ ታሪክ መዘከሪያ ብቻ አይደለም፣ ይልቁንም በክርስቶስ ኅብረት ማደግ፣ በመንፈስ መመላለስ፣ በምስጋና ሕይወት በፍቅርና በልግስና መኖርን የምንማርበትና በሕይወት የምንገልጥበት በዓል ነው። የንስሐ ሕይወትና ይቅር ባይነትም የመስቀል በዓል ጥሪዎች ናቸው። በመሆኑም እንደ ደመራው በአንድ ላይ ተሰባስበን፣ እንደ ብርሃኑ በሰው ሁሉ ፊት የክርስቲያናዊ ምግባራችንን ብርሃን ልናሳይ ይገባል።

በመስቀሉ ስቦ ወደራሱ ያቀረበን አምላክ በዓሉን የሰላምና የደስታ በዓል ያድርግልን፤ የመስቀሉ ኀይልና በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን!

# አባ ሳዊሮስ

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ
ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ዋና ሥራ አስኪያጅ
የደቡብ ምዕራብ ሸዋና የሸገር ከተማ
አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

መስከረም ፲፮ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ



# የብፁዕ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ መልእክት

"በመስቀሉ ለክርስቶስ ተሞዐ ሞት÷ ወተቀጥቀጠ አርዑተ ኀጢአት፡- በክርስቶስ መስቀል ሞት ተሸነፈ፤ የኀጢአትም ቀንበር ተሰበረ።"

(ድጓ ዘመስቀል ገጽ 27)

በሥነ ፍጥረት ታሪክ ውስጥ በሰው ልጅ ተፈጥሮና ጸጋ ልክ የከበረ ሌላ ፍጥረት የለም። በኵረ ፍጥረታት አዳምን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋና ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ አዋሕዶ፥ ፈጥሮ፥ በልጅነት አክብሮ፥ በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ሾሞት እንደነበር በቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጧል፡ ፡ ይሁን እንጂ ሰው በተሰጠው ክብርና ጸጋ፥ ሳይደክም ባገኘው ኑሮና ሀብት ብዙ መቆየት አልቻለም። (ዘፍ. 2÷7)

በኤደን ገነት በተድላ፥ በሐሴት በሚኖርበት ቦታ የተሠራለትን ሕግ ጥሶ ፈጣሪውን በማሳዘኑ ከፍታው በውድቀት፥ ክብሩ በሐሣር፥ ሕይወቱ በሞት ተለወጠ። ዕፀ በለስን እንዳትበላ፤ እሷን ከበላህ ትሞታለህ! ብሎት ነበርና ትእዛዙን ተላልፎ ዕፀ በለስን በመብላቱ ሞት ተፈረደበት።

# “የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”

በምክረ ሰይጣን ከፈጣሪው ተለያይቶ ኀይለ ጽልመት በሰፈነባት፥ የጨለማ አበጋዝ በነገሠባት እሾህና አሜከላ በምታበቅለው ምድር ሊኖር ስደተኛ ሆኖ ከገነተ ተድላ ወጣ። ከጸአተ ገነትም በኋላ ነፍሱ በሞት ግዛት፥ ሥጋው በመቃብር ድቅድቅ ጨለማ ባለበት መካነ ደይን በጽኑ ሕማምና በብዙ ጩኸት ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ቆየ።

ተስፋ ድኅነቱ ሊፈጸም ጊዜው ሲደርስ “ፈነወ እግዚአብሔር ወልዶ ወተወልደ እምብእሲት ከመ ይሣየጦሙ ለእለ ውስተ ኦሪት፤ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ልጁን ላከ።” (ገላ. 4÷4)

በአባቱና በመንፈስ ቅዱስ፥ በራሱም ፈቃድ ሊያድነን የመጣው፥ የጽድቀ ኦሪት ፍጻሜ የሆነው፥ ከባሕር እስከ ባሕር እስከ ዓለም ዳርቻ የሚገዛው መኰንነ ጽድቅ ክርስቶስ የሚያምኑት ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ሞትን አሸንፎ የጨለማውን ገዢ ሊያስወግድ በማእከለ ምድር ቀራንዮ ተሰቀለ። (ሮሜ 10÷4፤ መጽ/ምሥጢር ገጽ 54 )

በመስቀሉም ለአዳምና ለልጆቹ ሞትና ስደት ምክንያት የነበረው ሰይጣን ድል ተነሥቷል፥ የኀጢአት ቀንበር ተሰብሮአል፤ ሞት ተሸንፎ፥ ኃይለ ጽልመት ተገፎ የሰው ልጅ ክብሩና ማዕረጉ ተመልሶአል።

ቀድሞ የተዋረደው፥ በመስቀሉ ኀይል ወደ ክብሩ የተመለሰው ሥጋችንም ከብሮ አምላክነትን አግኝቶ በየማነ አብ፥ በዘባነ ኪሩብ ተቀምጦአል። ይህ ድንቅ ምሥጢር የተፈጸመበት፥ ሞት የተሸነፈበት፥ መስቀሉ በዚህ ዓለም ስንኖር ኀይለ ጸላዒ የምናደክምበት፥ ለክብረ ትንሣኤ የምንበቃበት፥ ነገረ ድኅነትን አጉልተን የምናሳይበት የመዳናችን አርማ ነው።

‹‹እስመ ፈቀደ በዝንቱ ከመ ይንስት ጥበቦ ለሰይጣን፤ እግዚአብሔር ወልድ የሰይጣንን ምክር በዚህ ያፈርስ ዘንድ›› የመረጠው ዕፀ መስቀሉ አርዑተ ኀጢአት የተሰበረበት፥ ዓለም የተቀደሰበት ስለሆነ በድኅነታችን ውስጥ ሰፊ ደርሻ ያለው ነው።

መስቀሉና በእርሱ ላይ የፈሰሰው የማይነጥፈው ደሙና ውኃውም ወደ ጥንተ ሕይወታችን የተመለስንበት፥ ከቁጣው የዳንበት ዐቢይ ምሥጢር መሆኑን ቅዱስ አትናቴዎስ ‹‹ዝ ውእቱ ዘአጥፍኦ ለሞት ወሠዐሮ ለዲያብሎስ፤ ሞትን ያጠፋው፥ ዲያብሎስን የሻረው እርሱ ነው›› በማለት ገልጦታል።

ድኅነተ ሰብእን በተመለከተ በሕግ የተጻፈው፥ በነቢያት የተነገረው ሁሉ በመስቀሉ እንዲህ ባለ ሁኔታ በመጠናቀቁ “አሜሃ መልአ ፍሥሓ አፉነ ወተሐሥየ ልሣንነ -- ያንጊዜ አፋችን ደስታን፥ አንደበታችን ሐሴትን ሞላ” ስደተኛው ሰይጣን አፈረ፥ በእኛም መዳን የመዓርግ መዝሙር ተዘመረ። (መዝ. 126÷2)

ከበሮውን አንስተን፥ ደስ የሚያሰኘውን በገና ከመሰንቆው ጋር አዋሕደን ከምናቀርበው የክብር ዝማሬም ጋር ወደ ጥንተ ሕይወት የተመለሰንበት መስቀለ ክርስቶስ ለእኛ ለኦርቶዶክሳውያን “አዐትብ ገጽየ ወኵለንታየ በትእምርተ መስቀል” እያልን በማማተብ ሰይጣንን የምንክድበትና የምናሳድድበት ጽንዐችንና ኃይላችን ነው።

የሞት ሥልጣን የተሻረበትን፥ መኰንነ ጽልመት ዲያብሎስ የተሰደደበትን በዓለ መስቀሉን በየዓመቱ ስናከብር ሰይጣንና ሥራው የሚገለጥባቸው ተግባራት ከእኛ በእውነት ተሰደዋል? ወይስ ከእኛ ጋር አሉ? የሚለውን ሕይወታዊ ጥያቄ ከመመለስ ጋር መሆን ይኖርበታል። ምክንያቱም የመስቀሉ ውበት፥ የክርስትናው ታሪካዊነት የሚገለጠው የእኛ ሕይወት ከጠብና ከክርክር ነጻ ሆኖ፥ በፍቅር ተስተካክሎ እንዲኖር ማድረግ ሲቻል ነው።

በመሆኑም የማመን መንፈሳዊ ትርጉሙ የሚለካው ያመነ ሰው ለተሟላ ሰላም፥ ለማኅበራዊ ፍትሕ፥ ለሀገር አንድነትና ደኅንነት፥ ለእኩልነትና ለነፃነት በሚያደርገው ተሳትፎ ነውና በመለያየት ጥፋት እንጅ ልማት ሊመጣ እንደማይችል ተገንዝበን፥ ጥላቻን አስወግደን ግብዝነት በሌለበት ፍቅር ሆነን በዓለ መስቀሉን ማክበር ይገባናል።

ከሰይጣን ግዞት በመስቀሉ ነጻ ያወጣን
መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሀገራችንን ከጥፋት÷
ሕዝባችንን ከስደት ይጠብቀልን፤
ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን በአንድነቷ ያጽናልን።

መልካም የመስቀል በዓል ለሁላችን ይሁንልን።

**አባ ዲዮስቆሮስ**
የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና
የራያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ



# የመንፈሳዊ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ መልእክት

"ወኲሉሰ እምኀበ እግዚአብሔር ዘአቅረበነ ኀቤሁ በክርስቶስ ወወሀበነ መልእክተ ሠምረቱ እስመ ተዋለጠ እግዚአብሔር ዓለመ በክርስቶስ፤ የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን÷ የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚ አብሔር ነው፤ እግዚአብሔር ዓለምን በክርስቶስ ዋጅቶአልና።"
(2ቆሮ. 5÷18፡19)

ይህ ጥቅስ በእግዚአብሔር አብና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስሙን ይሸከም ዘንድ ለሐዋርያዊ ተልእኮ የተጠራው ቅዱስ ጳውሎስ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ስለ ታላቁ ዕርቅ ያስተማረው ትምህርተ መለኮት ነው:: ዕርቅ ከተነሣ ዘንድ የቆየ ጠብ እንደነበረ መረዳቱ አያዳግትም፤ በእርግጥም ከክርስቶስ መስቀል በፊት ሰማያትንና ምድርን ያካለለ ከባድ ጠብ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ነበረ::

ቅዱስ መጽሐፍ ይህንን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡ - ‹‹ወሶበ እንዘ ፀሩ ለእግዚአብሔር ንሕነ ተሣሃለነ በሞተ ወልዱ፤ የእግዚአብሔር ጠላቶቹ ሳለን በልጁ ሞት ታረቀን ወይም ይቅር አለን›› (ሮሜ 5÷10):: በመጀመሪያው በሰው በደል ምክንያት በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የጠብ መገለጫ የሆነው መለያየት ተፈጥሮአል፤ የጠቡ መነሻ፦ ሰው በእግዚአብሔር ሕግ ላይ የፈጸመው በደል ነው:: እግዚአብሔር በባሕርዩ በደልን ከቶ የማያነጻ፤ ኀጢአተኛውንም የማያጸድቅ አምላክ ነው (ዘፀ. 23÷7):: እግዚአብሔር በደልን ወይም ኀጢአትን እንዲሁ ማለፍ የማይችልበት ዋናው ምክንያት፦ መልካም ለሠራ ዋጋ፥ ሳጠፋ ደግሞ ፍዳ የሚያመጣና የማያዳላ እውነተኛ ዳኛ በመሆኑ ነው:: እግዚአብሔር እውነተኛ የፍርድ ጠባቂና አስጠባቂ፥ በቃሉ የጸና፥ ቃሉና ተግባሩ፥ ሕጉና ፍርዱ በትክክል የሚፈጽም፥ የዳኞች ሁሉ የበላይ ዳኛ ነው:: በመሆኑም ሰው በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ ሆኖ ሲገኝ መቀጣቱ የማይቀር ነበር:: ከዚህ አኳያ በእግዚአብሔር አሠራር በደለኛን መቅጣት እንጂ ዝም ብሎ ማለፍ የማይታሰብ ስለሆነ ሰው ተቀጣ፤ ቅጣቱም የሰው ነፍስንና ሥጋን፥ ምድርንና በውስጧ ያለውን ሁሉ ያጠቃለለ ነበረ:: «ካንተ የተነሣ ምድር የተረገመች ትሁን›› የሚለው ቃሉም ይህንን ያረጋግጣል::» (ዘፍ. 3÷17)::

የቅጣቱ ዋና ጭብጥ ‹‹ሞትን መሞት ነበር››፤ ሰውም በቅጣቱ መሠረት በምድርም በሰማይም ሟች ሆነ ማለትም በምድራዊ ሕይወቱም ሆነ በሰማያዊ ሕይወቱ ከእግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ከሆነው ክብርና ሕይወት ሁሉ ተለየ:: የቅጣቱም ሁኔታ በዚህ ልክና መጠን ተግባር ላይ ዋለ:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እውነተኛ ዳኛ እንደሆነ ሁሉ የፍቅርና የጥበብ ባለቤት ስለሆነ በፍጹም ፍቅሩና ጥበቡ ሰውን ሊታረቀው ፈቀደ::

## “የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”

የዕርቁን ፍንጭም የቅጣቱን ፍርድ ባስተላለፈበት ጊዜ አሳየ፤ እንዲህ ብሎ፦ «አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ፤ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» (ዘፍ. 3÷22)። ይህ የዕርቅ ተስፋ የኋላ ኋላ ሰብአዊ ክዋኔያችን በተዋሕዶተ ቃል ወደ እግዚአብሔርነት ክብር እንደሚመጣ የሚጠቁም ነበረ። ከዚህ ጀምሮ እግዚአብሔር ተስፋውን በየጊዜው በአበው ነቢያት እየገለጸ ሰውን ሲያጽናና ኖሮአል፤ በመጨረሻም እንደ ተስፋ ቃሉ ቀዳማዊ ቃል ወልደ እግዚአብሔር ወይም ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ሰብአዊ ክዋኔያችንን በምልአት ተዋሕዶ ሰው ሆነ። በዚህ አኳኋን ሰብአዊ ክዋኔያችን በሦስትነቱ ርባዔን ሳያስከትል በተዋሕዶተ ቃል በመንበረ ጸባዖት መቀመጥ ቻለ። «አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» የሚለው የዕርቁ የተስፋ ቃልም በዚህ ጊዜ በተግባር ተተረጐመ።

በሌላ አባባል ሰውነታዊ ክዋኔያችን ከቃል ጋር ሲዋሐድ በቃል ርስትነት እግዚአብሔር ሆነ ማለት ነው። በዚህ ምሥጢረ ተዋሕዶ እግዚአብሔርም ሰውም የሆነው እግዚአብሔር ቃል፡- ኢየሱስ ክርስቶስ፥ መድኀኔ ዓለም፥ አማኑኤል በሚል ስም ተጠራ፤ በዚህ ሁኔታ ዓለምን ወይም ሰውን ከእግዚአብሔር የማስታረቅ ተግባር ተጀመረ። የዕርቁ ተግባር በማሕፀነ ድንግል ማርያም በተከናወነው ቅፅበታዊ ተዋሕዶ ተጀምሮ በመስቀሉ ላይ በፈጸመው የቤዛነት መሥዋዕት ተጠናቀቀ። ሆኖም የቤዛነቱ አድኅኖ እስከ ጌታችን ቀን ወይም እስከ ዕለተ ምጽአት ይቀጥላል፤ በመሆኑም ትልቁ የዕርቅ ተግባር የተፈጸመው በመስቀል በተሰቀለ ቀን ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ እግዚአብሔር በእርሱ መሥዋዕትነት እኛን ከራሱ ጋር አስታርቆአል፤ በደላችንንም መቍጠሩን ትቶአል፤ ምክንያቱም በበደለኞቹ በእኛ ፈንታ ክርስቶስ የሞታችንን ቅጣት ተቀብሎአልና ነው። በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር በክርስቶስ ቤዛዊ ሞት ታረቀን፤ እግዚአብሔር በሁሉም ነገር ፍጥረቱን የሚያሳትፍ አሳታፊ አምላክ ነውና ለእኛም የማስታረቅ አገልግሎት ሰጠን። ዋናውና ታላቁን ዕርቅ በውድ ልጁ ደም ቢፈጽመውም ከዚያ በመለስ የሚፈጸሙ ብዙ የዕርቅ ዓይነቶች ስላሉ በእነሱ ሰውን ማገልገል እንችል ዘንድ ለእኛም የማስታረቅ አገልግሎት ሰጠን።

ከዚህም የተነሣ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን፤ የመስቀሉ ነገር ዕርቅና ሰላም ነው። በሰማይና በምድር የሚሠራ ዕርቅ፥ በነፍስም በሥጋም የሚገለጥ ዕርቅ፥ የማያቋርጥ ዘላለማዊ ዕርቅ፥ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበን ዕርቅ ነው። እዚህ ላይ ሁላችንም መመለስ ያለብን ጥያቄ የዕርቅ አገልግሎት እንድንፈጽም እግዚአብሔር አዞናል፤ መብቱንም ሰጥቶናል፤ ግን አገልግሎቱን በትክክል እየሄድንበት ነው ወይ? የሚለውን ነው። ይህ ለክርስቲያኖች ሁሉ የቀረበ ጥያቄ ነው፤ ክርስቲያኖች ይህንን ጥያቄ የመመለስ ግዴታ አለብን።

ይህንን ሳንመልስ መስቀልን ብናከብር፥ ብንሳለምና ብንዘምር በእግዚአብሔር ፊት ያለው ተቀባይነት አናሳ ከመሆን አያመልጥም። እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ዕርቅና ፍቅርን፥ ሰላምና አንድነትን ይወዳል፤ በመስቀል ላይ የተሰቀለው እነዚህን ለማስፈን ነው። ለእነዚህ ሲባል እንከን የለሽ ደማዊ መሥዋዕት ተከፍሎአል። እንግዲያውስ ለዕርቅና ፍቅር፥ ለሰላምና አንድነት ሲባል እስከ ሞት ድረስ የሚዘልቅ መሥዋዕትነት ልንከፍል የማስታረቅ አገልግሎት ከእግዚአብሔር ዘንድ ተሰጥቶናልና በተግባር እንፈጽመው። ክርስቲያኖች ልናረጋግጠው የተፈለገው ዕርቅና ሰላም ራስን እስከ ሞት ድረስ በመስጠት እንጂ ሌላውን በመግደል እንዳይደለም ልብ ይሏል። ገዳዮች ከሆንማ በደለኞች እንጂ አስታራቂዎች ልንሆን አንችልም። የክርስቲያኖች አስታራቂነት ዘርፈ ብዙና ሰፊ ነው፤ ሰውን የምናስታርቀው፦ ከእግዚአብሔር፥ ከራሱ፥ ከሰውና ከአካባቢው ጋር ነው።

ይህ ከሆነ ምድራችን በፍጹም ሰላም ትሞላለች፤ የእግዚአብሔር ሰላም ተብሎ በቅዱስ መጽሐፍ የሚነገረን እንዲህ ያለው ሰላም ነው፤ ማለትም ከእግዚአብሔር፥ ከራሳችንና እንዲሁም ከፍጥረት ሁሉ ጋር የምናደርገው ዕርቀ ሰላም ማለት ነው።ከዚህ ውጭ የሚነገረው ሰላም ጎዶሎ እንጂ ምሉእ ሊሆን አይችልም። ስለሆነም ከእግዚአብሔርም፥ ከራሳችንም፥ ከሥነ-ፍጥረትም ጋር በትክክለኛው ዕርቅ እንታረቅ። ይህ ዓይነት ዕርቅም በሀገራችንና በዓለም እንዲሰፍን ከእግዚአብሔር የተሰጠንን የማስታረቅ አገልግሎት በትጋት እንፈጽም፤ «የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው» ተብሎአልና።

“ወለእግዚአብሔር አኰቴት

ዘወሀበነ ንማዕ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ”

**ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ**

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላዩ ቤተክህነት

የመንፈሳዊ ዘርፍ ዋና ምክትል ስራ አስኪያጅ



# የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ መልእክት

“ተዘከሩ መዋዕለ ትካት፥ ወሐልዩ ዓመተ ትውልደ ትውልድ፥ ተሰአሉ ለአቡከ ወይነግረከ፥ ወለሊቃውንት ወይዜንውከ፡- የዱሮውን ዘመን አስብ፤ የብዙ ትውልድንም ዓመታት አስተውል፤ አባትህን ጠይቅ፥ ያስታውቅህማል፤ ሽማግሌዎችህን ጠይቅ፥ ይነግሩህማል።”

(ዘዳ. 32፥7)

ሀገራችን ኢትዮጵያ የጥንታዊና ሐዋርያዊ አስተምህሮ፥ የትውፊትና ሥርዐት፥የባህልና የቅርስ መገኛ የሆነች ሀገር ናት። ለረጅም ዘመናት የተጠበቀና ከትውልድ ወደ ትውልድ ለሚተላለፍ ዕውቀትና ጥበብም ባለቤት ናት።በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተጻፉና ከተለያዩ ቋንቋዎች የተተረጐሙ ቅዱሳት መጻሕፍትም በጥንታውያን አድባራትና ገዳማት ተጠብቀው ይገኙባታል። ኢትዮጵያ በዚህ ደረጃ በምትነሣበት ጊዜ ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የዚህ ሁሉ ጥንታዊ ሀብትና ጸጋ ምንጭ ሆና

ትነሣለች፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጥንቱ ዘመነ ሐዋርያት ከተመሠረቱ ጥቂት ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት አንዷ እና ቀዳሚዋ ናት፡፡ ከጥሩ ሐዋርያዊ ምንጭ ከሚቀዳ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ በተሠራ ርቱዕ ሃይማኖት ለሰው ልጆች ድኅነት ከመቆም በተጨማሪ የትምህርት፥ የባህል፥ የሥነ ጥበብና የኪነ ሕንጻ፥ የሌሎችም የዕውቀትና የጥበብ ሀብቶች መገኛ ሆና ባለመለወጥ ለዘመናት የኖረች ይህች ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡

በዓላት የሚከበሩበት ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ሥርዐት ሰላምን ይሰብካል፥ ኅብረትን ያጠናክራል፥ ሀገራዊ አንድነትንም ያጸናል፡፡ በዓለ ቅዱስ መስቀል ይህን የመሰለ ይዘት ካላቸው በዓላት መካከል ዋንኛው ነው፡፡ በዓሉ ረጅም ታሪክ ያለውና አባቶቻችን ጠብቀው ያቆዩልን ሀብታችን ነው፡፡ ይህን የመሰለ አኩሪ ታሪክና ሀብት ባላቸው አብያተ ክርስቲያናት ለሚገኝ ሕዝብ የሚመከረው ነገር ቢኖር ቀጣይነት ነው፡፡ የተነሣንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልም የሚያስተላልፈው መልእክት ተመሳሳይ ነው፡፡

የቀጣይነት ጥሪ ያለፈውን የረሳ ወይም በአግባቡ ያልተጠቀመበት የአዲስ ነገር ብቻ ናፋቂ ትውልድ ሲመጣ የሚተላለፍ ነው፡፡ ይህም ትናንትን ለማሰብና ለማወቅ ብቻ የሚተላለፍ ጥሪ ሳይሆን፥ የዛሬ ማንነትን በጠንካራ የሃይማኖትና የታሪክ መሠረት ላይ ለመገንባት ጭምር ነው፡፡ "የዱሮውን ዘመን አስብ፤ የብዙ ትውልድንም ዓመታት አስተውል፤ አባትህን ጠይቅ፥ ያስታውቅህማል፤ ሽማግሌዎችህን ጠይቅ ይነግሩህማል" የሚለው ቃል በመነሻው እስራኤል የተደረገላቸውን እየረሱ በተቸገሩ ጊዜ የተላለፈላቸው መልእክት ነው፡፡ ትናንትን እንዲያስቡ ይመክራቸዋል፡፡ ለእኛም አባቶቻችን ጠብቀው ያቆዩልንንና ለቀጣዩ ትውልድም ልናስተላልፈው የሚገባውን የበዓል አከባበር ሥርዐት አስመልክቶ የሚመክረን ነገር አለው፡፡ በአንዳንዶቻችን ዘንድ በዓሉ እንደ ልማድ እየተቆጠረ መንፈሳዊ ፋይዳው ይዘነጋል፡፡ አንዳንዶች ደግሞ አስተምህሮአዊ ይዘቱና ታሪካዊ መሠረቱ ተረስቶ ዘመን እንዳመጣው እንግዳ ባህል ይወሰዳል፡፡

ነገር ግን የመስቀል በዓል መሠረቱ ከቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ ጋር በጥልቀት የተያያዘ፥ የሃይማኖት ተግባራዊ መገለጫ ነው፡፡ ቅዱስ ኤፍሬም ቅዱስ መስቀሉን በገነት ከነበረው ዕፀ ሕይወት ጋር እያነጻጸረ ያስተምር ነበር፤ 'በዕፀ መስቀል ላይ ተሰቅሎ ሕይወት እንድናገኝ አደረገን፡፡ በገደለን ዛፍ ፈንታ ሕይወት የሚሰጠውን ዛፍ አገኘን' ብሏል (Hymns on the Crucifixion)፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፦ 'ቅዱስ መስቀል ከፀሐይ ይልቅ የሚያበራ፥ ከነገሥታት ዘውድ ይልቅ የከበረ፥ ተስፋና ግርማችን የሆነ …' ይለዋል (Homilies on First Corinthians)፡፡ ቅዱስ ያሬድ፦ 'ዮም መስቀል ተሰብሐ ለአኀው አብርሀ፥ ዮም መስቀል እምፀሐይ ወእምከዋክብት አብርሀ -- ዛሬ በመስቀል ለወንድሞች ተገለጠ፤ ከፀሐይና ከከዋክብት ይልቅ አበራ' ማለቱ፥ የአስተምህሮ አንድነትና ቀጣይነትን የሚያሳይ ነው፡፡ ሁሉም ቅዱሳን አበው ስለ ቅዱስ መስቀሉ ክብር አስተምረዋል፤ ጽፈዋል፡፡

በታሪክ ረገድም ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጋር የተያያዘ፥ የንግሥት ዕሌኒን ፍለጋ የተከተለ፥ ከጠፋበት፥ ከተቀበረበት ወጥቶ መክበሩንና ከፍ ከፍ ማለቱን እየዘከረ የቀጠለ ታላቅ በዓል ነው፡፡ አውሳብዮስ ዘቂሳርያ (Life of Constantine, Book 3)፥ ሌሎቹም የታሪክ ጸሓፊዎች እንደሚነግሩን በዚያ ዘመን (4ኛው ክ/ዘ) መስቀሉ በታላቅ በዓል ይከበር ነበር፡፡ በኢትዮጵያም ከዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በብዙ ድካምና ጥረት ወደ ሀገራችን የገባበትንና በግሸን ደብረ ከርቤ የተቀመጠበትን ሂደት ተከትሎ በልዩና ደማቅ ሁኔታ የሚከበርበትን ይዘት ሠርቶ ይገኛል፡፡ አባቶቻችን የመስቀሉ ነገር ስለገባቸውና ክብሩን ስለተረዱት፥ ከምንም ነገር አብልጠው ቅዱስ መስቀሉን ሽተው አምጥተዋል፡፡ ታሪክ የሚቀጥልበትን፥ ሥርዐት የሚጸናበትን ነገር ሁሉ ሠርተውልናል፡፡

ስለዚህ እኛም ልጆቻቸው የብዙ ትውልድን ዓመታት አስተውለን፥ አባቶቻችንን ጠይቀን፥ ከሽማግሌዎች ተረድተን፤ የቀደመውን ሳንረሳ፥ በዓለ መስቀልን በመንፈሳዊነት ልናከብረው፥ ቀጣይነትን ልናረጋግጥና የአባቶቻችን ልጆች መሆናችንን ልናሳውቅ ይገባል፡፡ በረከተ መስቀሉ አይለየን!

**ረዳት ፕሮፌሰር ቀሲስ ግርማ ባቱ**

በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላዩ ቤተ ክህነት

የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ



# "መስቀል ኀይልነ፤ መስቀል ኀይላችን ነው::"

"እስመ ነገረ መስቀሉሰ እበድ ውእቱ በኀበ ኅጉላን ወበኀቤነሰ ለእለ ድኅነ ኀይለ እግዚአብሔር ውእቱ፤ የመስቀሉ ነገር በሚጠፉ ሰዎች ዘንድ ስንፍና ነውና ለምንድነው ለእኛ ግን የእግዚአብሔር ኀይል ነው።"

(፩ቆሮ. ፩÷፲፰)

በመጋቤ ምሥጢር ፍሬስብሐት ዱባለ
የሊቃውንት ጉባኤ ም/ሰብሳቢ

ይህን ኀይለ ቃል የተናገረው በአሕዛብም፥ በነገሥታትም፥ በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነው ብሎ ጌታችን የመሰከረለትና በአምላካዊ ጥሪው ለወንጌል አገልግሎት የጠራው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው:: (የሐዋ.ሥራ ፱÷፲፭)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጻፋቸው መልእክታት ውስጥ ‹‹ቅዱስ መስቀል›› ለክርስትናው ዓለም የመኖሩ ምሥጢር፥ የሕይወቱ መሠረት፥ የሰላሙ ፋና፥ የጠላት ድል መንሻ፥ የኀጢአት መደምሰሻ መሆኑን በብዙ ቦታ ላይ በሰፊው ገልጾት እናገኛለን:: ቅዱስ ያሬድም ‹‹ዝንቱ መስቀል ቤዛነ መድኀኒትነ ለአይሁድ ስደተ ኮነ ወለነኒ ሕይወተ ኮነነ፤ ይህ ቅዱስ መስቀል ቤዛችንና መድኀኒታችን ነው፤ የመስቀሉ ጠላት ለሆኑት አይሁድ ስደታቸው ሲሆን፤ ለምናምነው ለእኛ ግን ሕይወታችን ነው» ብሎ አብራርቶታል:: (የመስከረም መስቀል አቡን)

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ሲል የተቀበላቸውን ሕማማተ መስቀል፥ የከፈለውን መሥዋዕትነት፥ የገለጸውን ፍጹም ፍቅር፥ ያወጀውን ዕርቅና ሰላም ስናስብ፥ መስቀልን ከሮማውያን የወንጀለኛ መቅጫነት አውጥቶ በክቡር ደሙ ቀድሶ ለዓለሙ ሁሉ መዳን ምንጭና መሠረተ ቤተ ክርስቲያን ስላደረገው፥ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በዓለ ቅዱስ መስቀልን በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዐት ታከብራለች:::

ወደ ዋናው ርእሳችን ከመሄዳችን በፊት ስለዚህ ታላቅ ሐዋርያ ትውልድና ለሐዋርያነት መመረጥ በመጠኑ መግለጽ አስፈላጊ ነው::

ይህ ታላቅ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ፥ ከአበ ብዙኃን አባታችን አብርሃም ዘር ከነገደ ብንያም የተወለደ እስራኤላዊ ሲሆን፤ ለሕገ ኦሪት ቀናተኛና ታማኝ ከመሆኑ የተነሣ ቤተ ክርስቲያንን አሳዳጅ እንደነበር እራሱ በጻፈው መልእክቱ፦ ‹‹ግዙር ዘበሳምንት እምሕዝበ እስራኤል እምነገደ ብንያም ዕብራዊ ዘእምዕብራውያን ወበሕገ ኦሪት ፈሪሳዊ ወበቅናት ሰደድኩ ቤተ ክርስቲያን በጽድቀ ኦሪት ንጹሐ ከዊንየ፤ በስምንተኛው ቀን የተገዘርሁ፥ ከእስራኤል ሕዝብ ከብንያም ነገድ ከዕብራውያን ዕብራዊ ነኝ፤ በኦሪትም ፈሪሳዊ ነበርሁ:: በኦሪት ጽድቅም ያለ ነውር ሆኜ በቅንዐት ምእመናንን አሳድድ ነበር» ብሎ አረጋግጦልናል:: (ፊልጵ. ፫÷፭:፮)

የቀድሞ ስሙ ሳውል ይባል የነበረው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሥርዐተ ኦሪት ያደገ፥ ሕገ ኦሪትን ከታዋቂው ምሁረ ኦሪት ገማልያል እግር ሥር ሆኖ በጥልቀት የተማረ ምሁር ነው:: መምህሩ ገማልያልም ምሁረ ኦሪት በመሆኑ ቅዱስ ጳውሎስም ከርእሱ በመማሩ እንደ መምህሩ ለሕገ ኦሪት ቀናተኛ እና ታማኝ እንደነበር ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክሩለታል:: ሐዋርያው ቅድይስ ጳውሎስ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ከዐረገ በኋላ ከአይሁድ ሽማግሌዎች ከምሁራነ አይሁድ ጋር ተባባሪ በመሆን ያገለግል ነበር::

ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዐረገ

## “የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”

በ፳ኛው ወር፥ አይሁድ የክርስቶስን መከራ መስቀል ለመሸከም ዝግጁ ሆኖ ስለ ወንጌል ሕይወቱን ለመስጠት የቀረበውን ቅዱስ እስጢፋኖስን በድንጋይ ወግረው ሲገድሉ፥ ለቅዱስ እስጢፋኖስ መገደል ተባባሪ በመሆኑ፥ ገድለው እስኪመለሱ ድረስ ልብሳቸውን ሲጠብቅ የነበረ ይኸው አንጋፋ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ነው። (የሐዋ. ሥራ ፯÷፶፰)

በዚህ ወቅትም በእምነታቸው ጸንተው፥ የክርስቶስን መከራ መስቀል ተሸክመው ይጓዙ ለነበሩ ለስምንት ሺህ ማኅበረ እስጢፋኖስ የስደትና የመከራ ዘመን በመሆኑ፥ የማኅበሩ መሥራች ቅዱስ እስጢፋኖስ ከሞተ በኋላ እኒህ ማኅበረ እስጢፋኖስ በየሀገሩ ተበትነው እየዞሩ፥ በየምኵራቡ እየተገኙ ወንጌልን በማስተማራቸው ብዙ ሰዎችን በክርስቶስ እንዲያምኑና ክርስቶስን እንዲከተሉ አድርገዋል።

ከአሳዳጆቹም መካከል አንዱ በመጀመሪያ ለሕገ ኦሪቱ ታማኝና ቀናዒ (ቀናተኛ) የነበረው፥ በክርስቶስ ከተጠራ በኋላም ለወንጌል አገልግሎት ቈራጥ የሃይማኖት መዶሻ፥ መከራ መስቀሉን ለመሸከም ሌት ከቀን የሚተጋ፥ አስመሳዮች በበዙበት ዘመን አስመሳይነትን የሚጠላ ይህ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከሊቀ ካህናቱ የፈቃድ ደብዳቤ ተቀብሎ ማኅበረ እስጢፋኖስንም ሆነ በክርስቶስ ያመኑ ክርስቲያኖችን በደማስቆ በማሳደድ ላይ እንዳለ ምንም አሳዳጅ ቢሆንም ማእምረ ኅቡአት ከባቴ አበሳ የሆነው ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከአመነ በኋላ መስቀሉን ተሸክሞ በጽናት የሚጓዝ የእምነት ሰው፥ የወንጌል አርበኛ፥ ጠንካራ፥ ‹‹ሊከተለኝ የሚወድ መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ›› ያለውን አምላካዊ አደራ በተግባር የሚተረጉም መሆኑን በዐወቀ ገንዘብ ‹‹ሳውል ሳውል ለምንት ትሰድደኒ ወይቤሎ መኑ አንተ እግዚኦ ወይቤሎ አነ ውእቱ ኢየሱስ ናዝራዊ ዘአንተ ትሰድደኒ ይብእሰከ ረጊጽ ውስተ ቀኖት በሊኅ ወእንዘ ይርእድ ይቤሎ እግዚኦ ምንተኑ ትፈቅድ እግበር አነ -- ሳውል ሳውል ለምን ታሳድደኛለህ የሚለውን ቃል ሰማ፤ ሳውልም አቤቱ አንተ ማነህ አለው፤እርሱም አንተ የምታሳድደኝ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ፤ በሾህ ብረት ላይ ብትቆም ላንተ ይብስሃል አለው፤ እርሱም እየተንቀጠቀጠና እየፈራ አቤቱ ምን እንዳደርግ ትሻለህ? ...›› ሲለው ማድረግ ያለበትን ነግሮታል። የተነገረውንም በመስማት በሐናንያ አማካኝነት አምኖና ተጠምቆ የወንጌል አገልግሎቱን ጀምሯል። (የሐዋ.ሥራ ፱÷፬)

አገልግሎቱንም የጀመረው ከፍተኛ ዋጋ ከሚያስከፍሉት ከወገኖቹ አይሁድ በመሆኑ ይህ ነው የማይባል ግፍና መከራ የደረሰበት ቢሆንም ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ በመስቀል ላይ ሆኖ ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ ለሰው ልጅ የከፈለውን ጸዋትወ መከራ በዐይነ ሕሊና እያሰበ‹‹ተመሰሉ ኪያየ ከመ አነ እትሜሰሎ ለክርስቶስ -- እኔ ክርስቶስን እንደመሰልኩ እኔን ምሰሉ›› እያለ የክርስቶስን መከራ መስቀል ተሸክሞ አሳይቶናል።

ይህ ማለት ‹‹ዘኢጾረ መስቀለ ሞትየ ኢይክል ይጸመደኒ፤ መስቀሌን ተሸክሞ ያልተከተለኝ አገልጋዬ ሊሆን አይችልም›› በማለት፥ ጌታችን በቅዱስ ወንጌል መስቀል መከራ መሆኑን የመስቀልን ትርጉም ገልጾ ባስተማረው ትምህርት መሠረት ዛሬ ያለነውም ሆነ ወደፊት እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የሚነሣው ትውልድ ሁሉ በያለበት ቦታ፥ በያለበት ደረጃና ኀላፊነት እንደ ቅዱሳን ሐዋርያት እስከ ሞት ድረስ መስቀሉን ተሸክሞ የማይጓዝ ከሆነ፥ የክርስቶስ ተከታይ ሊሆን እንደማይችል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መስቀሉን ተሸክሞ በሕይወቱ አሳይቶ አረጋግጦልናል።

ለዚህም ከቅዱስ ጳውሎስ በተጨማሪ ምሳሌ የሚሆኑን የአምላካቸውን አሠረ ፍኖት በመከተል መከራ መስቀሉን ተሸክመው ከተጓዙት ቅዱሳን ሐዋርያት መካከል እነቅዱስ ጴጥሮስ ተዘቅዝቀው በመሰቀል፥ እነቅዱስ ቶማስ ቈዳቸውን በመገፈፍ፥ ሌሎችም ቅዱሳን ሐዋርያት በተለያየ መንገድ የመስቀሉን ጸዋትወ መከራ በመቀበል ተጋድሏቸውን ፈጽመው ለክርስትና መኀልበት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተው ያለፉ ቅዱሳን ምሳሌ ሊሆኑን ይገባል።

ዛሬም ቢሆን ክርስቶስን አሳልፈው ከሰጡ መካከል ተረፈ አይሁድ፥ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጥቅሟን የሚሹ፥ እሷን ግን የሚጠሉ እራስ ወዳዶች በውስጥም በውጭም እያሳደዷት በመሆኑ አደብ እንዲገዙ ሃይ ማለት እንደሚያስፈልግ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይመክረናል።

ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከላይ ከጠቀስናቸው የመስቀሉ ጠላቶች ሞኞችና ሰነፎች በመስቀሉ አማካኝነት መዳናችን ያመንን እኛን ለመለየት የቅዱስ መስቀሉን ነገር ሲያብራራ፥ የመስቀሉ ነገር በኢአማንያን ዘንድ ሞኝነትን መስሎ መሰናክልና ዕንቅፋት ሲሆንባቸው ለሚያምኑት ግን የእግዚአብሔር ኀይልና ጥበብ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር የዓለምን ኀይል፣ ጥበብና ዕውቀት ኢአማንያን በናቁትና በማያምኑበት መስቀል ከንቱ አድርጎታል።

ለቅዱስ መስቀሉ ጠላት ሆነው የተሰለፉ አይሁድም




‹‹መድኀኒቶሙ ጸልዑ፤ መድኀኒታቸውን ጠሉ›› እንዳለ ሊቁ፥ የሕይወት ምንጭ የሕይወት መገኛ የሆነውን አምላካቸውን ጠልተው ሰቅለው መግደላቸው ሳያንሳቸው፥ ጌታ የተሰቀለበትን ቅዱስ መስቀሉን መቅበራቸው ከሞኝም ሞኝ፥ ከሰነፍም ሰነፍ መባል የሚያንሳቸው እንጅ የሚበዛባቸው አይደለም፡፡

ደግሞ የሚያስገርመውና የሚያስደንቀው እነዚህ መስቀሉን የቀበሩ የመስቀል ጠላቶች የአይሁድ መሪዎች፥ የቤተ መቅደሱ ባለቤቶች ራሳቸው ድነው ሰውን እንዲያድኑ የታመነባቸው ባካሄዳቸው፥ባለባበሳቸውና ባነጋገራቸው ሁሉ የሚያፍራቸውና የሚያከብራቸው የድኅነትን በር ዘጊ ሆነው መገኘታቸው ነው፡፡

ዛሬም በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እየገጠመን ያለ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ዋጋ እየከፈሉ ያሉ መልካም እረኞች፥ ለመንጋው የሚጨነቁ መሪዎች እንዳሉ ሁሉ፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አሳድጋና አስተምራ ሥልጣነ ክህነት ሰጥታ፥ መስቀል አስጨብጣ በክህነቱ ክርስቶስን እንዲያገለግሉ፥ በመስቀሉ ምእመናንን እንዲባርኩ በሥልጣኑ ዶግማዋን፥ ሥርዐቷንና ቀኖናዋን እንዲጠብቁና እንዲያስጠብቁ ታላቅ ኀላፊነት የተሰጣቸው በጣት የሚቈጠሩ ጥቂት አካላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የሰጠቻቸውን ኀላፊነት ወደጐን በመተው በሙስና እየተዘፈቁ፥ ነውር እየፈጸሙ፥ የዋሃን ምእመናንን እያታለሉና በሚፈጽሙት ነውር እያሳዘኑ፥ በቅዱስ መስቀሉ እየነገዱ፥ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ነቅፈው ለነቃፊ፥ ሰድበው ለሰዳቢ አሳልፈው ሲሰጡ ማየት መስቀሉን ከቀበሩ፥ የድኅነት በርን ከዘጉ፥ ጌታቸውን ከሰቀሉ ከአይሁድ መሪዎች ያልተናነሰ የነውር ሥራ እየሠሩ መሆኑን ልብ ማለት ይገባናል፡፡

በመሆኑም በየደረጃው በኀላፊነት ያለን አካላት ከነዚህ በመስቀሉ ከሚነግዱ ጥቂት ነውረኛ ነጋዴዎች ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መጠበቅ ነገ ዛሬ የማይባል በፍጥነት የማስተካከያ እርምት መሰጠት ያለበት መሆኑን እየጠቆምን በየደረጃው ያለን የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆችም በዚህ ሳንሰናከል ክርስቶስ እኛን ተክቶ በመስቀል ላይ የከፈለውን ዋጋ በዐይነ ሕሊና በማየት በክርስትናችን መጽናትና ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን በመጠበቅ እንዲሁም



በማገልገልና በመንከባከብ ከፍተኛውን ድርሻ መውሰድ እንዳለብን ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ክርስትናችን ያስገድደናል፡፡

እንግዲህ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቊርሶ ዓለምን ያዳነበት ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስን ድል የነሣበት ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ጸጋው ተገፍፎ ሰላሙን አጥቶ አወዳደቁ ከፍቶ የነበረው የሰው ልጅ ሰላሙ የተረጋገጠበት፥ ነጻነቱ የታወጀበት፤ ነገር ግን ታሪኩ እንዳይነገር፥ ታምራቱ እንዲጠፋ የቤተ መቅደሱ መሪዎች ያስቀበሩት ቅዱስ መስቀል፥ በሚያምኑና በማያምኑ መካከል መለያ ምልክት ሆኖ ይታያል፡፡ይህ ማለት ቅዱስ መስቀል ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ሊያድን እንደ ተሰቀለ ሆኖ በእምነት መነጸር የምናይበት የድኅነታችን ምሥጢር ነው፡፡ (ገላ. ፫÷፩)

በሌላ በኩልም ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰማይና ምድርን፥ ሰውና እግዚአብሔርን፥ ሰውና መላእክትን፥ ነፍስና ሥጋን፥ ሕዝብና አሕዛብን በአጠቃላይ በሰማይም ሆነ በምድር በቀደመው አባታችን አዳም በደል ምክንያት ሰብሳቢ አጥቶ ተበታትኖ የነበረውን አንድ ያደረገበት የአንድነታችን ምሥጢር የተረጋገጠበት የሰላማችን ምንጭ ምልክታችን ቅዱስ መስቀል ነው፡፡

ይህንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መስቀል እውነተኛ ሰላም ያገኘንበት መሆኑን ሲገልጽ፦ ‹‹ወቦቱ ይሣህሎ ለኵሉ ወገብረ ሰላመ በደመ መስቀሉ ለዘበሰማይ ወለዘበምድር -- ሁሉንም በእርሱ ይቅር ይለው ዘንድ በመስቀል ባፈሰሰው ደም በምድርና በሰማያት ላሉ ሰላምን አደረገ›› ይላል፡፡ (ቈላስ. ፩÷፳)

እንደገናም፦ ‹‹አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል፥ እርሱ ሰላማችን ነውና፤ ሁለቱን ያዋሐደ፥ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ በሥጋው ያፈረሰ ሰላምን ያደርግ ዘንድ፤ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው፤ መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላም፥ ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን የምሥራች ብሎ ሰበከ›› ይላል (ኤፌ. ፪÷፲፫-፲፰)

ይህ ማለት ከጌታችን ስቅለት በኋላ የነጻነታችን ዐዋጅ የተበሠረበት ሰላማዊ ዙፋን በመሆኑ በመስቀሉ አማካኝነት ያገኘነውን የሰላም ምልክት ለምናምን ሁሉ የነጻነትና የድል ምልክታችን ነው፡፡ ምልክት ማለት የማይታየውን ነገር የሚገልጽና የሚያረጋግጥ ማለት ሲሆን፤ ጌታችንንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ረቂቅ የሆነውን የማዳን ጥበብን የገለጸበት ስለሆነ እንደዚህ ሐዋርያ ‹‹ወአንሰ ሐሰ ሊተ ኢይዜኀር ዘእንበለ በመስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ወበኀቤየሰ ምዉት ዓለም ወአነሂ ምዉት በኀበ ዓለም...እኔ ግን ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት እኔም ለዓለም ከተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ የምመካበት ነገር የለኝም›› ማለት ይገባናል፡፡ (ገላ. ፯÷፲፬)


ስቅለት

## “የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን እስራኤላውያንን ከባርነት ለማውጣት፥ ከታዘዘው መቅሠፍት ለማዳን፥ በቤታቸው መቃን ላይ የበጉን ደም ምልክት እንዲያደርጉ በማድረግ ከመቅሠፍት አድኗቸዋል (ዘፀ. ፲፪÷፲፫)። በኋላም በኀጢአታቸው ምክንያት ተናዳፊ እባብ ታዝዞባቸው እየነደፈ ሲያሠቃያቸው ይቅር እንዲላቸው ንስሓ ቢገቡ በሚታይ ቦታ ላይ የእባብ ምልክት በመስቀል አምሳል እንዲሰቅሉ በማድረግ ያነን እያዩ እንዲድኑ አድርጓቸዋል። (ዘኍ. ፳፩÷፰)

እነዚህ ነገሮች ለጊዜው ከሥጋ ሞት ለመዳን የሚያገለግሉ ቢሆንም ዋናው ዓላማ ግን በሐዲስ ኪዳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በአፈሰሰው ደሙ የሰው ልጅ ድኅነት የሚፈጸም መሆኑን ጠቋሚ ምልክት ሲሆን፤ ጊዜው ሲደርስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቈርሶ ሰውን ለፍጹም ድኅነት አብቅቶታል።

ዛሬም በቅዱስ መስቀሉ ፍጹም ድኅነት ያገኘን መሆናችን አምነን በተግባር ለማረጋገጥ፦ መስቀሉን፦ በልብሳችን፥ በአንገታችን፥ በአካላችን፥ በቤታችን የክርስትናችን ምልክት አድርገን ተሸክመነው እንገኛለን። ይህ መልካምና የሃይማኖታችን ማንነትን የሚገልጽ ምልክታችን መሆኑ ይበል የሚያሰኝ መልካም ተግባር ነው። ነገር ግን ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስን ወግቶ ለመጣል የተጠቀመበት ትልቁ መሣሪያ መስቀል መሆኑን ተገንዝበንና የመስቀሉ ፍቅር ገብቶን በሕወታችን እየተዋጋን ያለውን ክፉ መንፈስ የምናሸንፍበት ይህ መስቀል መሆኑን መገንዘብ ይገባናል።

በመሆኑም በየዓመቱ እያከበርነው ያለው ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎ ዓለምን ያዳነበት ቅዱስ መስቀል የበረከታችን ምንጭ ከመሆኑ አንጻር ከመስቀሉ በረከት ለመካፈል አስበን በልዩ ልዩ አገልግሎት ተሰልፈን በማገልገልና መስቀሉን በማክበር ላይ ያለን ሁሉ የመስቀሉ በረከት ተካፋዮች ሆነናል።

ምክንያቱም እንኳን የቅዱስ መስቀሉ ፍቅር በልቡናችን የተሳለብን፥ በመስቀሉ ኀይል እየተጠቀምን ያለንና የመስቀሉን በረከት ሽተን የመጣን እኛ፤ ውስጡ ጥበበ እግዚአብሔር ቢሆንም፥ በምቀኝነት የተነሡት አይሁድ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚሰቀልበትን መስቀል አሸክመው ሊሰቅሉት ወደ ጎልጎታ ሲወስዱት፥ በአጋጣሚ መንገድ ላይ ተገኝቶ መስቀሉን ያሸከሙት ቀሬናዊ ስምዖን የበረከቱ ተሳታፊ እድለኛ እሆናለሁ ብሎ ሳይጠብቀው የመስቀሉ በረከት ተሳታፊ ሆኖ አይተነዋል። (ማቴ. ፳፯÷፴፪)

በዕውቀት የበሰሉ፥ በሕገ ኦሪት የተካኑ፥ ትንቢተ ነቢያትን ጠንቅቀው ያወቁ ፈሪሳውያን በተደፈነ ልቡናቸው፥ በታወረ ዐይናቸው ጌታቸውን ለመስቀል ሲሯሯጡ፤ ዕድሜ ልኩን ሰዎችን በመዝረፍ፥ ቋንጃ በመቁረጥ፥ ደም በማፍሰስ መላ ዘመኑን ኀጢአት ሲሠራ የኖረው ፈያታዊ ዘየማን ‹‹ተዘከረኒ እግዚኦ አመ ትመጽእ በመንግሥትከ፤ አቤቱ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ» ብሎ በደቂቃዎች ውስጥ በገባው ከእውነተኛ ልብ በመነጨ ፍጹም ንስሓ ወደ ገነት ለመግባት የመጀመሪያው ሰው ሲሆን፤ ባጋጣሚ መንገድ ላይ ተገኝቶ መስቀሉን የተሸከመው ቀሬናዊ ስምዖንም ከመስቀሉ የሚገኘውን በረከት አግኝቷል። (ሉቃ. 23÷42)

በአጠቃላይ፤ ከዘመናት በፊት ተነሥቶ ስለ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለድና ዓለምን በመስቀሉ ቤዛነት ማዳን ትንቢት ሲናገር የቆየው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት፥ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን የተሰቀለበትና ደሙን አፍስሶ በደሙ የቀደሰው ቅዱስ መስቀል፥ ለሚፈሩትና ለሚያመልኩት የተሰጠ፥ የዓለምን መዳን የሚያመለክት የክርስትና ምልክት፥ የሰላም፥ የፍቅር፥ የዕርቅ፥ የአንድነትና የነጻነት አርማ ሆኖ እንደሚያገለግል፤ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋው የተፈተተበትን፥ ክቡር ደሙ የፈሰሰበትን፥ ዓለም የተቀደሰበትን በመሳለምና በመዳሰስ ሞትን ከሚያመጣ የሰይጣን ቍራኝነት ሁሉ ተላቀን ከኀጢአት ርቀን እርሱን መከላከያ ጋሻ አድርገን ተጠብቀን የምንኖርበት መሆኑን ሲገልጽ፦ ‹‹ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ ከመ ያምሥጡ እምገጸ ቅስት ወይድኀኑ ፍቁራኒከ፤ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው፤ ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ›› ብሎ የመስቀል ምልክት ከሞት ጦር የምናመልጥበት፥ የእግዚአብሔርን ሰላም የምናገኝበት፥ የነጻነታችን ምልክት፥ እውነተኛ የፍትሕ ዙፋን እንደሆነ በትንቢቱ ተናግሯል። (መዝ. ፶፱÷፬)

ቅዱሳን መላእክትም ሲፈጠሩ የበላይ አድርጎ የፈጠረው ሳጥናኤል በፈጣሪው ላይ በዐመፀ ጊዜ ከርእሱ ጋር የተዋጉ ብርሃናውያን መላእክት ሳጥናኤልን እስከ ሠራዊቱ ድል የነሡት ኀይል ይሆናቸው ዘንድ በየክንፋቸው የሳለባቸው የብርሃን መስቀል ኀይልና ጋሻ ሆኗቸው በመሆኑም እኛም ቅዱስ መስቀል ጋሻችን፥ ኀይላችን፥ ሰላማችንና ምልክታችን ቅዱስ መስቀል መሆኑን ተገዝበን የበረከቱ ተሳታፊ እንድንሆን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጥሪዋን ታስተላልፋለች። የመስቀሉ በረከት አይለየን።



# መስቀል በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት

በመጋቤ ምሥጢር አእመረ ፀሐዩ (MA)
የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የግዕዝና የሥነ ጽሑፍ መምህርና የትምህርት ክፍል ኀላፊ

የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አርኣያና አምሳል የተፈጠረ ክቡር ፍጥረት እንደሆነ በዘፍጥረት ምዕ. ፩ ቊ. ፳፮ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ሁሉም ፍጡር እግዚአብሔርን ማየት የማይቻለው ቢሆንም፥ በአርኣያው የፈጠረውን ሰው በማየት ስለ እግዚአብሔር መልክና አምሳል ማወቅና መናገር ይችላል፡፡ (ዮሐ. ፩÷፲፰)

የሰው ልጅ ቆሞና ሁለት እጆቹን ወደ ጐን ዘርግቶ ስንመለከተው የመስቀል ቅርፅ አለው፤ አርኣያ እግዚአብሔርንም በዚህ አንጻር በዐይነ ሕሊና ስንመለከተው መስቀለኛ ነው ብንል ሐሰት አይሆንም፡፡ ስለሆነም ዕፀ መስቀል ከዕፅነት ባለፈ የእግዚአብሔር መልክ የሚገለጽበት ምሥጢር ነው፡፡

መስቀል ከሰው ልጅ ውድቀትና ድኅነት አንጻር ሲታይ ደግሞ፥ሔዋን ሕግ ጥሳ የበላችው ዕፀ በለስ ምክንያተ ሞት ሲሆን፥ ዕፀ መስቀል ምክንያተ ሕይወት ሆኗል፡፡ አዳኙ መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ ሲሆን፤ መስቀል ምክንያተ ድኅነት ነው እንላለን፡፡ በዚህ መሠረት ሃይማኖተ አበው የሚባለውን መንፈሳዊ መጽሐፍ የተናገሩ፥ የጻፉ፥ ያዘጋጁና ሌሎችም ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ስለ መስቀል ምን አሉ? የሚለው የዚህ አጭር ጽሑፍ መነሻ ነው፡፡ መልካም ንባብ!

«ውእቱ ዝንቱ መስቀል ዘቦቱ ንትመካሕ ከመ ንሰብሖ ቦቱ፤ እንስግድለት ዘንድ የምንመካበት መስቀል ይህ ነው፡፡» (ሃይ.አበ. እልመስጦአግያ ፬÷፫)

የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ በቅዱስ መጽሐፍ እንደ ተጻፈው፥ «የምንመካበት መስቀል» እግዚአብሔር የድል አርማ፥ ምክንያተ ድኅነትና መግረሬ ፀር አድርጎ፥ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ ያከበረውን መስቀል ጋሻ መከታ አድርገን እንኖራለን በማለት የመስቀልን ክብር ከመገልጽ ባሻገር፥ ለመስቀል የጸጋ ሰግደት እንደሚገባ የሚያስረዳ ጭብጥ ነው፡፡

አይኑ መንክር ዘይደሉ ከመ ናንክር እምኔሁ ፈድፋደ... በትርኑ ዘአንቅዐ ማየ እምኰኵሕ ወሚመ መስቀል ዘአንጽሐ ዓለመ፤ እጅግ ልናደንቅ የሚገባው ድንቅ ነገር የትኛው ነው? ከዐለት ውኃ ያፈለቀው የሙሴ በትር ነው? ወይስ ዓለምን ያከበረ መስቀል ነው? (ሃይ.አበ. ኤራቅሊስ ፵፰፥፵፮)

ሊቁ ኢራቅሊስ፦ ተዋርዶ የነበረ ዓለም የከበረበት፥ ዕፀ በለስን በልቶ ቅድስናውን አጥቶ የነበረ የሰው

# “የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”

ልጅ የተቀደሰበት መስቀል ነው ይላል፡፡ ከዐለት ውኃ ያፈለቀችውን የሙሴን በትር እናድንቅ? ወይስ ዓለም የከበረበትን መስቀል እናድንቅ? በማለት በንጽጽር ይናገራል፡፡

በሙሴ በትር የፈለቀው ውኃ ከሥጋ ጥም የሚያረካ ነው፤ በመስቀል ላይ ከተሰቀለው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጎን የፈሰሰው ማየ ገቦ ግን ከጽምአ ነፍስ የሚያረካና ዘለዓለማዊ ሕይወትን የሚሰጥ ነው የሚል ቃል በአንክሮ ያስተምራል፡፡ በዚህ ገጸ ንባብ የትኛውን እናድንቅ? በሚል ንጽጽር የቀረቡ ሌሎች ፅንሰ ሐሳቦች ቢኖሩም፥ ለርእሰ ጉዳዩ ንጽጽር ተሰማሚዎቹ ‘በትርና መስቀል’ ናቸው፡፡ ስለሆነም ጽሑፉ ሁለቱን ያነጻጽራል፤

በብሉይ ኪዳን በሙሴ በትር ምክንያት የታዩት ተአምራት ለድኅነተ ሥጋ ብቻ ናቸው፤ የተደረገውም ለእስራኤል ዘሥጋ ነው፡፡ በእግረ መስቀሉ የታዩት ተአምራት ግን ለድኅነተ ነፍስ ማለትም ለዘለዓለም ሕይወት መገለጫ ናቸው፡፡ መስቀል የሐዲስ ኪዳን በግ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሠዋበትና በደሙ ያከበረው ስለሆነ እንደ ሙሴ በትር አምሳል መርገፍ ሳይሆን አማናዊ የሐዲስ ኪዳን የድል አርማ ነው፡፡

«ቃላ ለሔዋን ከሠተ ዕፀ ወበውእቱ ዕፅ ወፅአ አዳም እምገነተ ተድላ ወቃልሰ ዘተወልደ እምድንግል ከሠተ መስቀለ፤ የሔዋን ልብላ ማለቷ ዕፀ በለስ ምክንያተ ሞት መሆኑን አስረዳ፤ ከድንግል የተወለደ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ግን መስቀል ምክንያተ ሕይወት እንደሆነ አስረዳ፡፡» (ሃያ.አበ. ዮሐንስ አፈወርቅ ፷፯÷፳)

ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ መስቀል ምን አለ? ቢሉ፥

ሔዋን ዕፀ በለስን በመብላቷ የሰው ልጅ ከገነት ፈለሰ፥

ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሰቀሉ ዓለም ተቀደሰ፡፡

ዕፀ በለስ አዳም ከነልጅ ልጆቹ ለአምስት ሺሕ አምስት መቶ ዘመናት በሞት ጥላ ሥር እንዲኖር ምክንያት ሆኗል፡፡ ዕፀ በለስ ሲነሣ በአእምሯችን የሚታወሰው ስሕተት፥ ጥፋት፥ ኀዘን፥ ጸጸት፥ መከራና ሞት ነው፡፡ በአንጻሩም ዕፀ በለስ ሲወሳ አብራ የምትወሳው ሔዋን ናት፡፡ የስሕተት ጀማሪ፥ መሪና ፊታውራሪ መሆኗን አእምሯችን ያውጠነጥናል፡፡ “መስቀል” በማለት ስሙ ሲዘከር ግን፥ በብሉይ ኪዳን ሰዎችን ሰቅሎ መግደያ ያደርጉት የነበረው አሉታዊ ትውስታ በአእምሯችን አይታሰብም፡፡ ይልቁንስ መስቀል ሲባል በምናባችን የሚቀረፀው ብርሃን፥ ደስታ፥ የድል ስሜት፥ የፈውስ ስሜት፥ ሕይወትና ድኅነት ነው፡፡

ከሃይማኖታዊው ይዘት ወጥተን ዓለም አቀፍ የነፍስ አድን ድርጅት መለያ አርማ የሆነውን “ቀይ መስቀል” ስናስብ፥ በተንቀሳቃሽ መኪናዎቹ ላይ ተለጥፎ ስናይ በአእምሮአችን የሚሳለው ከሞት አፋፍ የደረሰችን ሕይወት የሚታደግ የሕይወት አርማ እንደሆነ ነው፡፡ ስለሆነም ዮሐንስ አፈወርቅ ዕፀ በለስ ምክንያተ ሞት፥ ዕፀ መስቀል ደግሞ ምክንያት ሕይወት በማለት ነገረ መስቀልን ያስተምረናል፡፡

«ሐመ ከመ ሰብእ በሥጋሁ አንዘ ኢየሐምም በመለኮቱ ዘውእቱ ረኀብ ወጽምዕ ሞት በሥጋሁ ቅዱስ ዲበ ዕፀ መስቀል ቅዱስ ዘተወክፎ ለመድኀኒተ ዚኣነ፤ በመለኮቱ ሳይታመም ሰው በመሆኑ ታመመ የተቀበለውም መከራ መራብ፥ መጠማት ነው፤ ይህም እኛን ለማዳን ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ ክቡር ደሙን አፍስሶ በተሰቀለበት በቅዱስ መስቀል ላይ ነው፡፡» (ሃይ.አበ. ቴዎዶስዮስ ፹፸÷፳፩)

ሊቁ ቴዎዶስዮስ መስቀልን “ቅዱስ” በማለት ገልጾታል፤ ቅዱስ ማለት በሰዋስዋዊ ፍቺው፦ ንጹሕ፥ ልዩ፥ ክቡርና ምስጉን ማለት ነው፡፡ ንጹሕ አለው፦ ንጹሐ ባሕርይ ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዐርብ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ በደሙ ቀድሶታልና፡፡ ልዩ አለው፦ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ ንጉሡ ዕፀዋት አድርጎታልና፡፡ ክቡር አለው፦ የተዋረደው የሰው ልጅ በመስቀል ላይ በተሰቀለው በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቀደመ ክብሩ ተመልሷልና፡፡ ምስጉን አለው፦ “መስቀል መልዕልተ ኵሉ ነገር” ብሎ ቅዱስ ያሬድ አመሰግኗልና፡፡

«እስመ ሕማማት እንተ ተወክፉ ኢትፈልስ ኀበ ሙስና ዘውእቱ ረኃብ ወጽምዕ ወድካም … ወስቍረተ እደዊሁ ንጹሓት ወእገሪሁ ቅዱሳት ወተቀንዎቶሙ በዲበ ዕፀ መስቀል ማሕየዊ፤ በሥጋ የተቀበለው መከራ በመለኮቱ አላገኘውም፥ ይህም በሥጋ የተቀበለው መከራ፦ መራብ፥ መጠማት፥ መድከም … የንጹሓን እጆቹና የክቡራት እግሮቹ ሕይወት በተገኘበት በመስቀል ላይ መቸንከር መወጋት ናቸው፡፡» (ሃይ.አበ. ኪራኮስ ፺፩÷፴፯)

ቅዱስ ኤፍሬም ቅድስት ድንግል ማርያምን “የሕይወት ፍሬ ከአንቺ ዘንድ ተገኘ” ብሏታል፤ እውነት ነው! የዓለሙ ሁሉ ሕይወት በማኅፀኗ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ተፀንሶ፥ በኅቱም ድንግልና ተወልዶ ከሞት ወደ ሕይወት መልሶናልና፡፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ፍሬ ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስን ስለወለደች ሕይወት የተገኘባት ምክንያተ ሕይወት ትባላለች፡፡ እንደዚሁም ሁሉ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ክብርት ነፍሱን ሰጥቶ አዳምን ከነልጅ ልጆቹ

## “የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”

ያዳነበት የሕይወት መንገድ በመሆኑ ሊቁ መስቀል ዕፀ ሕይወት ሲል ይገልጸዋል፡፡

መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዐርብ በመስቀል ላይ ሆኖ በእግረ መስቀል ቆሞ ለነበረው ለቅዱስ ዮሐንስም “እናትህ እንኋት” ብሎታል፤ ለእመቤታችንም “ልጅሽ ይኸው” የሚሉ የተስፋ ቃላትን ተናግሯል፡፡ ስለዚህም ነው በሊቃውንቱ አንደበት፦ መስቀል ሕይወት የተገኘበት፥ የተስፋ ቃል የተፈጸመበት ምክንያተ ሕይወት የተባለው፡፡

«ርኅበ ወጸምዐ … ወተቀነወ እደዊሁ ወእገሪሁ ዲበ ዕፀ መስቀል ክቡር ወሃቤ ሕይወት፤ ተራበ፥ ተጠማ፤ እርሱ ሕይወትን የሚሰጥ ሲሆን በክቡር መስቀል ላይ እጆቹንና እግሮቹን ተቸነከረ፡፡ (ሃይ.አበ. ዮሐንስ ፶፲፫÷፱)

በክቡር መስቀል ላይ እጆቹንና እግሮቹን ተቸነከረ፤ በዚህ ኀይለ ቃል የተነገረው የመስቀል ክቡርነት ለመስቀል ክብር እንደሚገባው ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ሊቃውንት አባቶቻችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ክቡር መሆኑን በትምህርተ ሃይማኖታቸው አስተምረዋል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ምዕ. ፲፫ ቍ. ፯ ላይ «ወለዘሂ ክብረ አክብሩ፤ ክብር ለሚገባው ክብር ስጡ» ይላል፤ እኛ ኦርቶዶክሳውያንም ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክቡር ደሙ የቀደሰውን መስቀል እናከብራለን፤ ትእምርተ ክርስትና፥ ትእምርተ ድኅነት፥ ትእምርተ ኀይልና ትእምርተ መዊእ ስለሆነ፡፡

ስለ ነገረ መስቀሉ በቅዱሳት መጻሕፍትና በሊቃውንት አንደበት ተነግሮን፥ የመስቀሉ ክብር ገብቶን በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት፥ በመስቀሉ ምክንያተ ድኅነት ያመንን የክርስቶስ ቤተሰቦች ነን፡፡ ሌሎች ከዚህ በተቃራኒ ያሉ ወገኖች የመስቀሉ ክብር ላይገዳቸው ይችላል፤ ስለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፦ «እስመ ነገረ መስቀሉሰ እበድ ውእቱ በኀበ ህጉላን ወበኀቤነሰ ለእለ ድኅነ ኀይለ እግዚአብሔር ውእቱ፤ የመስቀሉ ነገር ላልገባቸው ሰዎች ሰንፍና ነው፤ በክርስቶስ ለዳንን በመስቀሉ ኀይል ለተማፀንን ለእኛ ግን የእግዚአብሔር ኀይል ነው» (፩ኛ ቆሮ. ፩÷፲፯) ብሎ የተናገረው፡፡

### መስቀል በኢትዮጵያዊው ሊቅ በቅዱስ ያሬድ

«በፍጽም ወበእንግድኣ በአጻብእ ወበመዝራዕት ትእምርተ መስቀል ጸዊረነ ናንሶሱ፤ በግንባራችን፥ በደረታችን፥ በእጃችንና በክንዳችን ትእምርተ መስቀሉን ተሸክመን እንመላለስ፡፡» (የመስቀል ድጓ)




መስቀል ለኦርቶዶክሳውያን እንደ አማራጭ ሳይሆን ከመላው አካላችን ጋር በመንፈስ የተዋሐደ፥ ከዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን ጋራ የተዛመደ መሠረታዊና መንፈሳዊ አርማችን ነው ይላል ቅዱስ ያሬድ፡፡ ስለዚህም ነው እናቶቻችን፥ እኅቶቻችን በግንባራቸው፥ በአንገታቸው፥ በደረታቸው፥ በእጃቸውና በእግራቸው በመስቀለኛ የሚነቀሱት፤ እንዲሁም በቀሚሳቸው፥ በነጠላቸውና በልዩ ልዩ ልብሶቻቸው በተለያየ ክር በቀይ ሐር በመስቀልኛ እየጠለፉ ይለብሳሉ፤ ከወርቅ ከብርና ከነሐስ በተለያየ የመስቀል ቅርፅ አሠርተው በአንገታቸው፥ በጆሮአቸውና በእጃቸው መዋቢያ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም ከሥጋዊ ውበት ባለፈ ነገረ መስቀሉን ይሰብካሉ ማለት ይቻላል፡፡

«መስቀል ብርሃን ለኵሉ ዓለም መሠረተ ቤተ ክርስቲያን፤ መስቀል ለዓለሙ ሁሉ ብርሃን ነው፤ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንም መሠረት ነው፡፡» (የመስቀል ድጓ)

## “የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”

መስቀል ለምን የዓለም ብርሃን ተባለ? ቢሉ፥ በኀጢአት የጨለመውን ዓለም፥ አምስት ሺሕ አምስት መቶ ዘመን በድቅድቅ የመከራ ጨለማ የነበረውን ዓለም በሕይወት ብርሃን የታደገው ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎበት ዓለምን ስለአዳነ ነው ይሏል፡፡ ዘበጸዳለ ብርሃኑ ሰሰለ ጽልመት እንዳለ ሊቁ፡፡ መስቀል መሠረተ ቤተ ክርስቲያን የተባለበትም ምሥጢር የቤተ ክርስቲያን መሠረት የተጣለው ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ በዕለተ ዐርብ በቀራንዮ አደባባይ በመስቀል ላይ ሲሰቀል እንደሆነ የሚያስረዳ ነው፡፡

ሌላው የመስቀል መሠረትነት ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም እንደ ተመሠረተች ቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራሉ፡፡

«ሄመክሙ መንፈስ ቅዱስ ጳጳሳተ ከመ ትርዐዩ ቤተ ክርስቲያኑ ለእግዚአብሔር እንተ አጥረያ በደሙ -- በደሙ የዋጃት የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ወይም ምእመንን ትጠብቁ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ጳጳሳት አድርጎ ሾማችሁ፡፡» (የሐዋ.ሥራ ፳÷፳፰)

ቤተ ክርስቱያን የተመሠረተችው በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደመ ወልደ እግዚአብሔር ስለሆነ ቅዱስ ያሬድ መስቀል የቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው ማለቱ ትክክለኛ አገላለጽ ነው፡፡

በመስቀሉ አርጎወ ገነተ በመስቀሉ ገብረ መድኀኒተ ገብረ ሰላመ፤ በመስቀሉ የገነትን በር ከፈተ፤ በመስቀሉ ድኅነትን አደረገ፤ በመስቀሉ ሰላምን አድረገ፡፡ (የመስቀል ድጓ)

ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመናት የተዘጋው የገነት በር የተከፈተው እግዚአብሔር ወልድ በመስቀል ላይ እንደተሰቀለ፥ በቀኙ በኩል ተሰቅሎ ለነበረው ጥጦስ ለሚባለው ወንበዴ በተናገረው የምሕረት ቃል መሆኑን ያስረዳል፡፡ ያን ጊዜ ጥጦስ፦ “እኛ የተሰቀልነው በኀጢአታችን ምክንያት ነው፤ አንተ ግን በደል የሌለብህ የሰማይና የምድር አምላክ ነህና አቤቱ በመንግሥትህ በምትመጣበት ጊዜ አስበኝ” አለው፡፡ በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደሆነ “አንተ አዳምን ቀድመህ ወደ ገነት ትገባለህ” አለው፤ በዚህ ሰዓት የገነት በር ተከፈተ፡፡ ይህን መሠረት አድርጎ ቅዱስ ያሬድ “በመስቀሉ የገነትን በር ከፈተ” አለ፡፡ «በመስቀሉ ለክርስቶስ ተሞአ ሞት ወተቀጥቀጠ አርዑተ ኀጢአት፤ በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ሞት ተሸነፈ፤ የኀጢአት ቀንበርም ተሰበረ፡፡» (የመስቀል ድጓ)

ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ፥ ብዙ ጸዋትወ መከራ ተቀብሎ፥ አዳምን ከነልጅ ልጆቹ ወደ ቀደመ ክብሩ የመለሰበትን ምሥጢር መናገር ነው፡፡ የኀጢአትን ቀንበር ሰበረ አለ? ዲያብሎስ አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ ሔዋን አመቱ ለዲያብሎስ ብሎ በእብነ ሩካም ጽፎ በዮርዳኖስ ወንዝ ጥሎ የነበረውን የዕዳ ደብዳቤ ኢየሱስ ክርስቶስ በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ሲጠመቅ እንደ አምላክነቱ እንደ ገል ቀጥቅጦ፥ እንደ ሠም አቅልጦ፥ እንደ ሰውነቱ በእግሩ ረግጦ መደምሰሱን ያስረዳል፡ ፡ «ወደምሰሰ ለነ መጽሐፈ ዕዳነ፤ የዕዳ ደብዳቤአችንን አጠፋልን፡፡» (ቈላስ. ፪÷፲፬)

«ዮም መስቀል አሠነየ ዓለመ እንተ በልየ በሥነ ማርያም አዋከየ ለክርስቲያን ከኖሙ ዕበየ፤ መስቀል ያረጀውን ዓለም ዛሬ አደሰ፤ በድንግል ማርያም ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ አበራ፤ ለክርስቲያን ክብር ሆነ፡፡»

መስቀል በብሉይ ኪዳን የሚታወቀው በወንጀለኛ መቅጫነቱ ነበር፤ በሐዲስ ኪዳን ግን መስቀል በኀጢአት ጉስቍሎ የነበረው ዓለም የታደሰበት የሰላም ምልክት፥ የሰላም ተምሳሌት፥ የዓለምን መጥፎ ገጽታ ያሳመረ የክርስትና ውበት እንደሆነ ቅድስ ያሬድ ያስተምራል፡፡

“በድንግል ማርያም ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ አበራ” ማለት መስቀል ብርሃን ተብሎ እንዲጠራ ያደረገው ራሱ ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተሰቀለበት ነው፤ ብርሃን የተቀመጠበት ነገር ከሌላው የበለጠ የብርሃኑ ሙቀትም ሆነ ብሩህነቱ ይቀርበዋል፡፡ መስቀልም እውነተኛ ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት፥ መዐዛ መለኮቱ መንበረ ብርሃን በመሆኑ የተነገረለት ኀይለ ቃል ነው፡፡ ቅድስ ያሬድም ሆነ ሌሎቹ ሊቃውንት ስለ ቅዱስ መስቀል የተናገሩት ነገር በአመዛኙ ተመሳሳይና ተቀራራቢ ነው፡፡

ሐሳቡ ሲጠቃለል፤ መስቀል ትእምርተ ሰላም፥ የድል አርማ፥ የዓለም ክብር፥ ምክንያተ ድኅነት፥ ትእምርተ ክርስትና፥ ቅዱስ፥ የሕይወት መንገድ፥ የጠላት ዲያብሎስ ድል መንሻ፥ ተባርከን የምንቀደስበት፥ ተዳሰን የምንፈወሰበት፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ደሙን ያፈሰሰበትና መዐዛ መለኮቱ ያረፈበት፥ መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ ለሰው ልጆች ድኅነት ሲል የተቀበለውን ጸዋተወ መከራ የምንዘከርበት፥ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኞች ሕይወት ጋራ የጠበቀ የሕይወት መስተጋብር ያለውና የነጻነት አርማ አድርገን የምንመካበት መስቀል እንደሆነና ለክብረ መስቀል የጸጋ ስግደት እንደሚገባ ሊቃውንቱ አስተምረዋል፡፡

ምንጭ፦- ሃይማኖተ አበውና የቅዱስ ያሬድ ድጓ፡፡




“ቀራንዮ ስሙ ለውእቱ መካን፤ የቦታው ስም ቀራንዮ ነው።”
ማቴ. 27፡33 (ቅዱስ ያሬድ)

መጋቤ ብርሃናት አባ ተክለ ያሬድ ጎርጎርዮስ (ቆሞስ)
የቅዱስ ሲኖዶስ ም/ዋና ጸሐፊ

የአዳም የራስ ቅል መካነ ድማኀ፥ ዳግማዊ አዳም የተሰቀለበት በደሙ የከበረ ምድረ ንጽሕ ቀራንዮ የያዘውን ረቂቅ ሐሳብ (የመዳን ምሥጢር) ጥልቅ በሆነ የተመስጦ ምልከታ፥ በውሳጣዊ ብርሃነ ልቡና ዕይታ ፈጽሞ ለመረዳት ብዙ ይቀረናል፡፡ በዚህ አጭር የጽሑፍ አምድም አጠቃሎ ማቅረብ የማይቻል መሆኑ ይታወቃል፡፡

የመስቀሉን (የቀራንዮን) ነገር የሚጀምረው እንጂ ተናግሮ የሚጨርሰው አንደበት፥ ጽፎ የሚያጠቃልለው የቃላት ውበት እንደሌለ፤ ሲታሰር የሚጽፈው፥ ሲፈታ የሚያስተምረው ቅዱስ ጳውሎስ የፍቅር ምዕራፍ በመባል በሚታወቀው መልእክቱ ሲናገር፦ ‹‹ነአምር ንስቲተ በበገጹ፤ ከዕውቀት ከፍለን እናውቃለን›› ብሎ ገልጦታል፡፡ (1ቆሮ. 13÷9፤ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ)

የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ክርስቶዶሉም የማይመረመር ልደቱን፥ የራስ ቅሉና መስቀሉ የተገናኙበትን ምሥጢር፦ ‹‹ጥበቡ ልዕልት ዘኢትትነገር፤ የማትመረመር ረቂቅ ጥበቡ›› በሚል ሲገልጠው፤ የሀገራችን መተርጉማን ደግሞ፦ ‹‹ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይረቃል›› በማለት ተርጉመውታል፡፡

በድኅነተ ሰብእ ታሪክ ሰምና ወርቅ ሆነው ያሉትን የራስ ቅሉንና የመስቀሉን ነገር ታሪካዊና ሥነ መለኮታዊ በሆነ ዐውደ ትርጓሜ የሚገልጡትን ሐሳቦች በቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃነት ፈልፍሎ ማውጣት መብራቱን መቅረዝ ላይ ማኖር ማለት ነው፡፡

በመሆኑም ይህን ረቂቅ ጥበብ በእግረ ደቂቅ እየተጓዝን ታሪኩን ከምሥጢሩ፥ ምሥጢሩን ከታሪኩ ሳንለይ አዋ ሕደን፥ በደም ያጌጠውን የክብር ጌታ፥ የማይከፈለውን ውለታ፥ በመጠኑ ለማየት እንሞክራለን፡፡ (ኢሳ. 63÷1፤ ዮሐ 19÷17፤ 1ቆሮ 2÷8)

# “የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”




**ቀራንዮ፡-** ታሪኩና መልእክቱ ከመተርጉም በላይ ቢሆንም፥ ፊደላዊ ትርጓሜው የአዳም ራስ ቅል የተቀበረበት፥ አይሁድ የፋሲካ በግ በሚሠዉበት የኒሳን ወር አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ለመሥዋዕት ያዘጋጀበት በምድረ እስራኤል ከሚገኙት ተራራዎች ሁሉ ፈጽሞ የተለየ የጭንቅላት ቅርጽ ያለው ትኩረት የሚስብ ቦታ ማለት ነው፡፡ ምሥጢራዊ ትርጉሙ ደግሞ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ልኮ እኛን የማዳኑን ዕቅድ የፈጸመበት፥ የሞት ሥልጣን በኀይለ መስቀሉ የተሻረበት፥ ፈውስ የሚያስፈልገው፥ በኀጢአት የደረቀው ቁስለኛው የራስ ቅልና የሚፈውሰው መስቀል የተገናኙበት ጥልቅ ትርጓሜ ያለው ትምህርተ ክርስትና ነው፡፡ (ሮሜ 8÷4)

ሁልጊዜ በማይዘነጋው የትምህርተ ክርስትና ሐተታም

ሲብራራ፦ የቀራንዮ ስያሜ ከታሪክ አልፎ አዲሱ የመንግሥተ ሰማያት ሕይወት በዚያ እንደሚጀመር የሚያሳይ የአዳም ራስ ቅል የለመለመበት ጥልቅ የሆነ ምሥጢር ያለው መሆኑን እንረዳለን፡፡ (ቈላስ. 2፥10፤ ቅዱስ ባስልዮስ)

## የራስ ቅል የለመለመበት ግሩም ምሥጢር፦



# “የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”

በቀራንዮ ተገብረ ሥርዓተ ምሥጢር በኢየሱስ ክርስቶስ ለሊሁ ቍርባን ወመስቀሉ ምሥዋዕ፤ በቀራንዮ የምሥጢር ሥርዐት በኢየሱስ ክርስቶስ ተደረገ፤ እርሱ ቍርባን መስቀሉ መሠዊያ ሆነ›› በማለት ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እንደነገረን፤ ሥጋው የተቆረሰበት፥ ደሙ የፈሰሰበት ቀራንዮ የአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን የሕይወት ቋጠሮ የተፈታበት ግሩም ምሥጢር ተፈጽሞበታል፡፡ ከሥጋና ከደም ያልሆኑት፥ ረቂቃን አጋንንት ድል የተነሡበት ምሥጢር ሲታሰብም ‹‹ዕፁብ ነገሩ በእንተ መስቀሉ፤ የመስቀሉ ነገር ዕፁብ ነው›› የሚባለው ለዚህ ነው፡፡

ምሳሌው የሚሆን ይስሐቅ የመሥዋዕቱን እንጨት በጀርባው እንደ ተሸከመው፥ ኀጢአት የማያውቀው ዳግማይ አዳም ዕፀ መስቀሉን ተሸክሞ በቪያዶሉሮሳ (በሕመሙ መንገድ) ሲጓዝ ወድቀ ወኢተንሥአ ኵሉ ዓለመ በቅጽበት ዘአቀመ፤ ዓለምን ሁሉ በቅጽበት የአጸናው መስቀሉን ተሸክሞ ወደቀ፤ ነገር ግን አልጠፋም፡፡ (ቅዱስ ያሬድ)

እርሱ ሰላማችን ነውና ‹‹እሬሲ መድኀኒተ ወአግህድ ቦቱ፤ መድኀኒትን አደርጋለሁ፥ እገለጥበትማለሁ›› ብሎ አስቀድሞ ትንቢት በአስነገረበት ‹‹የራስ ቅል›› በተባለው ተራራ፥ ጥልን በመስቀሉ ገድሎ ሕዝብና አሕዛብን አንድ ሊያደርግ እጆቹን ቀኝና ግራ ዘርግቶ ተሰቀለ፡፡ (መዝሙር)

‹‹ተሰቅሎ ወተረጊዞ ገቦሁ አውሐዘ ሎቱ ለአዳም ደመ ወማየ ወአጥለላ ለርእሱ ዘሀለወት በቀራንዮ ቅርብተ ታሕተ መስቀሉ፤ ቀራንዮ ተሰቅሎ ጎኑን ተወግቶ ለአዳም ከጎኑ ደምና ውኃን አፈሰሰለት፤ በመስቀሉ ሥር ተቀብራ ያለች የራስ ቅሉም አለመለማት፡፡» (መዝገበ ሃይማኖት 5÷35 )

በታሪክ፥ በገጸ ምድርና በሥነ ጽሑፍ ጥናት ልብን የሚነካ ጥልቅ የሆነ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ምሥጢር ባለው፥ የደረቀው ራስ ቅል በለመለመበት ቀራንዮ በመስቀሉም ፍጥረተ ሰብእ ሞትን ካመጣበት ኀይለ ኀጢአት ነጻ እንዲወጣ ኀጢአትን በሥጋው ኰነነው፡፡ (ሮሜ 8÷3፡4)

የሞትና የሲኦል መክፈቻ በእጁ የሆነለት፥ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ የተሠዋው በግ የከበረ ደሙን በቀራንዮ ላይ አፍስሶ የቤዛነቱን ሥራ በመፈጸሙ የተሰቀለ ሰው ሲሞት ባልተለመደ ሁኔታ በታላቅ ድምጽ ጮኾ ‹‹ተፈጸመ›› አለ (ዮሐ. 19፤ ራእ. 13÷8)፡፡ በምክረ ከይሲ የጠፋው ውበት የተገኘበት፥ የመስቀሉ ዓለማ ‹‹ተፈጸመ›› የተባለበት ግሩምና ድንቅ ምሥጢር የተፈጸመበት የቦታው ስም ቀራንዮ ነው፡፡ (ራእ. 5÷12)





“የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”

## በምድሪቱ ፍሬ የተገኘው፥ የማይጠፋው ውበት፦



ልዑለ ቃል ኢሳይያስ አስቀድሞ ‹‹በዚያ ቀን የእግዚአብሔር ቍጥቋጦ ለጌጥና ለክብር፥ ሳመለጡ ሰዎች የምድሪቱ ፍሬ ለትምክህትና ለውበት ይሆናል›› በማለት በመንፈስ ትንቢት እንደተናገረው፥ በምድሪቱ ፍሬ (በቅድስት ድንግል ማርያም) የማይጠፋው ውበት ተገኝቷል፡፡ (ኢሳ. 4÷2፤ 44÷3፤ ቅዱስ ያሬድ ጾመ ድጓ ገጽ 380፤ ቅ/ አባ ጊዮርጊስ አርጋኖን 4÷15)

‹‹ይሤኒ ላሕዩ እምውሉደ ዕጓለ እመሕያው፤ ውበቱ ከሰው ልጆች ሁሉ ያምራል›› ተብሎ የተነገረለት የዚያ ድንቅ ጌታ ውበት፥ ከጨካኞቹ የሮማ ወታደሮች ግርፋትና ከመከራ መስቀሉ ጽናት የተነሣ ‹‹እንወደው ዘንድ መልክና ደም ግባት የለውም›› ወደሚለው ታሪክ፥ ከሕይወታችን ጋር ወደተሳሰረው ኩነት ተለውጦአል፡፡ (መዝ. 3÷2)

የፍጥረት ሁሉ ናፍቆት የሆነው አምላካችን በቀራንዮ መልኩንና ደም ግባቱን አጥቶ እኛን ለማስዋብ (ለመቀደስ) በተቀበለው መከራ መስቀል ጸሓፊ ወዴት አለ? መዛኙስ ወዴት አለ? ብለን እንደ ነቢዩ እስክንደነቅ

ድረስ ‹‹ንጉሡን በፍቅሩ ውበት›› ፊት ለፊት አይተነዋል፡፡ (ኢሳ 33÷17፤ ሮሜ 8÷19)

በዐይናችን ያየነው ሕይወታችን ተሰቅሎ፥ አሮጌው ሰውነታችን ተወግዶ መንፈሳዊ ውበታችንንና ልጅነታችንን አግኝተን ወደ ደስታው ሠርግ ለመግባትም የውበታችን ምሥጢር የሚጀምረው ክርስቶስን መልክና ደም ግባት ባሳጣው የእኛ ምትክ (ቤዛ) ሆኖ በተቀበለው ሕማማተ መስቀል ነው፡፡

በመሆኑም የምድሪቱ ፍሬ ሠርጉ ዓለም ክርስቶስ በፈቃዱ የተቀበለው መከራውና ሞቱ ውበት ያገኘንበት መሆኑን ቅዱስ ያሬድ በመኃልዩ ‹‹ኀስምት እንተ ሠነየት በሞትከ ወዓመት እንተ ግእዘት በጽፍዓትከ ይእቲ ተቤዘዎት በመስቀልከ ወተሰይጠት በደምከ፤ ደም ግባት ያልነበራት፥ በሞትህ የተዋበች፥ በጥፊ በመመታትህ ነጻ የወጣች ቤተ ክርስቲያን (ምእመን) እርሷ በመስቀልህ ዳነች፥ በደምህ ተዋጀች›› በሚል እርሱን ወደ መምሰል የቀድሞ መልካችን እንደተመለስንና ወደፊትም የሚጠብቀን ሰማያዊ ክብር ታላቅ መሆኑን ለመረዳት ቅርብ በሆነ ሥዕለ ትርጓሜ አብራርቶታል፡፡

በሰማያት በግርማው ቀኝ የተቀመጠው መድኅን በዕለተ ዐርብ በቀራንዮ በፈጸመው የቤዛነት ሥራ ‹‹ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ?›› በማለት ምስክርነቱን በደም ያተመው ቅዱስ ጳውሎስ የገለጠውንም ታላቅ ድል በተአምኖ የምንቀበለው እውነት ነው፡፡ (1ቆሮ. 15÷55፤ ዕብ.1÷3)

የፍኖተ መስቀል ማጠቃለያ ቦታ በሆነው ቀራንዮ የተገለጠው የመስቀሉ ፍቅር፥ በጎልጎታ የታየው የትንሣኤው ክብር፥ በጥልቅ ሸለቆ ራስ ላይ በረገፈችው የክብሩ ጌጥ የተገለጠው ምሥጢር የተፈጸመበት ያ ‹‹የራስ ቅል›› በኪዳኑ ደም የከበረበት የቦታው ስም ቀራንዮ ነው፡፡ (ኢሳ. 28÷11፤ ዕብ. 10÷29)

## የሕጉ ክስ የቀረበት፥ ያልተለወጠው፥ የክስ ጽሕፈት፡-

ከሕግ ርግማን የተዋጀንበት፥ በመስቀሉ ራስ ላይ የተጻፈው ‹‹ንጉሠ አይሁድ›› የሚለው ጽሕፈት ሠራዔ ሕግ ክርስቶስ ሕግ ተላላፊ እንደሆነ ለማሳየት ታስቦ የተጻፈ የክስ ጽሕፈት ሲሆን፤ ለእርሱ ግን የዘለዓለም ንግሥናው በዐደባባይ በትክክል የታወጀበት፥ በእኛ ላይ የነበረው፥ በትእዛዛት የተጻፈው የዕዳ ጽሕፈት የተደመሰሰበት አምላካዊ ጥበብ ነው፡፡ (ማቴ. 27÷37፤ ገላ. 3÷13፤ ቈላስ. 2÷14)

በሌላ በኩል ገዢውም ‹‹ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ›› የሚለውን የጽሕፈት ሰሌዳ በመስቀሉ ራስ ላይ የአስቀመጠው የሮማዊው ጲላጦስ፥ የግሪካዊው ሄሮድስ፥ የዕብራዊው ሊቀ ካህናት የቀያፋ ወገኖች ‹‹አይሁድ ነጻ የሚያወጣቸውን ንጉሣቸውን ሰቀሉ›› እያሉ የተጻፈውን መግለጫ እያነበቡ እንዲሳለቁባቸው ነው፡፡ (ትር.ወን.፤ ሕማማት)

የሞት ቅድመ አያት በሆነው ቅናት ደሙን ለማፍሰስ በመፍጠን አሳልፈው የሰጡት፥ አይሁድ የሮማውን ገዥ ‹‹ኢትጽሐፍ ከመዝ፣ እንዲህ አትጻፍ›› ሲሉት ‹‹ዘጸሐፍኩ ጸሐፍኩ፣ የጻፍኩትን ጽፌያለሁ›› ያለው ከእርሱ የተነሣ ሳይሆን የሥልጣናት ሁሉ ራስ ኀይል እንደነበር በትርጓሜ ወንጌል ተረጋግጧል፡፡ (ያዕ 1÷15)

ይህም ተአምር በቀራንዮ እንደተከናወነ ‹‹ኀይል አምላካዊ አገበረቶ ከመ ኢይወልጥ ዘንተ -- የጻፈውን እንዳይለውጥ ያስገደደችው አምላካዊት ኀይል በጲላጦስ ላይ ነበረች›› ተብሎ ንግሥናውን በሚገልጽ መንገድ ተተርጉሟል፡፡

በሰማይ ሦስት፥ በምድር ዐራት ተአምራት በመፈጸማቸው ስለ እኛ በቀራንዮ የተሰቀለው ሰው ብቻ እንዳልሆነና ለፍጥረታት ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ አምላክ እንደሆነ በዚህ ተረድተናል፡፡ (ትር.ወን. ዘደብረ ገሪዛን) በመስቀሉ ራስ ላይ የተቀመጠው ያልተለወጠው የክስ ጽሕፈት የሥልጣናት ሁሉ ራስ ንግሥናው የታወጀበት፥ የዕዳችን ጽሕፈት የተደመሰሰበት የቦታው ስም ቀራንዮ ነው፡፡

## የመከራው አልጋ፥ የሠርጉ ዐጸድ ቀራንዮ፡-

በተፈጥሮው የራስ ቅርጽ ያለው፥ የሦስቱን ራሶች በምሥጢር አቅፎ የያዘው ይህ ትኩረት ሳቢ ተራራ በዕለተ ዐርብ በፈሰሰው የኪዳን ደም ተቀድሶአል፡፡ የዐሥራ አራተኛው ክፍለ ዘመን የሥነ ጽሑፍ መቅረዝ በመባል የሚታወቀው አባ ጊዮርጊስም የቀራንዮን መቀደስ በሚገልጠው ድርሰቱ፦ ‹‹ቀራንዮ ተቀደሰት በደመ ኢየሱስ ክርስቶስ ጎልጎታ ተቀደሰት በሥጋሁ ንጽሕት በቀራንዮ ተተክለ ዐራተ ሕማሙ … ቀራንዮ ዐጸደ መርዓሁ፣ ቀራንዮ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ተቀደሰች፤ ጎልጎታ በሥጋው ከበረች፤ በቀራንዮ የመከራው አልጋ ተተከለች፤ ቀራንዮ የሠርጉ ዐጸድ ሆነች›› ብሎአል፡፡ (አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ)



ወደ በጉ ሠርግ ብፁዓን ተብለን የምንጠራበት፥ ሁሉም ሙሽራ የሚሆንበት የበጉ ሠርግ የተዘጋጀው በሠርጉ አጸድ ቀራንዮ መሆኑን ከዮሐንስ ራእይ ጋር አስማምቶ ሊቁ በዚህ መልኩ ገልጦታል፡፡ ከዘላለም ሞት፥ ከገሃነመ እሳት ለመዳን በጉን ከሚዋጉት ተለይተን፥ አውሬውን ድል ነሥተን ያጌጠውን ልብስ ከለበስን (የጽድቅን ሥራ ከሠራን) ዕንባችን ይታበሳል፥ ስድባችንም ይወገዳል ፡፡

በእርግጥም ጽድቃችንን እንዳንጥል እንጅ ‹‹በተቀደሰው ተራራ ጌታ እግዚአብሔር ከሰው ፊት ሁሉ ዕንባን ያብሳል፤ ስድብንም ከምድር ላይ ያስወግዳል›› ተብሎ እንደ ተጻፈው፥ በቀራንዮ መስቀል ዕንባችንም ታብሶ ትንቢቱ ቃል በቃል ተፈጽሟል (ኢሳ. 25÷7-9)፡፡ የትውልዱ መዳኛና የዕንባ ማበሻ በሆነው ተራራ (በቀራንዮ) ላይ የተፈጸሙትን ምሥጢራት ቋጥረው የያዙት የፈዋሹ፥ የተቀጠቀጠውና የተፈወሰው ራሶች ናቸው፡፡

## የፈዋሹ ራስ

ለገዳዮቹ የሚሞተውን፥ በመገረፉ ቍስል ቍስላችንን የሚፈውሰውን የሕይወት ራስ ሮማውያን ወታደሮች ለቅጣት በሚታጠቁት በማይሰበር ዘንግ መቱት፡፡ የክብርና የምስጋና ዘውድ የሚቀዳጀውን የሕይወት ራስ እርሱን የእሾህ አክሊል አቀዳጁት፡፡›› (ማቴ. 27÷29፤ 2ቆሮ. 11÷25)

በደል ያልተገኘበት ንጉሠ ነገሥት ክርስቶስ የራስ ቅሉ ከብዙ እሾህ በተጎነጎነው አክሊልና በሕማማቱ ምክንያት ‹‹የሕማም ሰው ደዌን የሚያውቀው፥ የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ የአኖረው ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል›› ተብሎ የተነገረውን ትንቢት እርሱ ራሱን ተመትቶ፥ በሥጋ አዳም ላይ የበቀለውን ሦከ ኀጢአት አስወግዶ ብዙዎቹን በማጽደቅ ፈጽሞታል፡፡ (ኢሳ. 53÷3-11)

የፍጥረት ሁሉ ራስ ክርስቶስ ራሱን በዘንግ በመመታቱ ‹‹በህየ ሰበረ ኀይለ ቀስት፣ የሰባሪውን ራስ (የሰይጣንን ሥልጣን) ሰበረ (መዝ. 75÷3)፡፡ የራስ ቅላችንን ያቆሰለው፥ ልባችንን የሰበረው የዕባቡ ራስ የተቀጠቀጠበትም የቦታ ስም ቀራንዮ ነው፡፡



## የተቀጠቀጠው ራስ፡-

የጥፋቱ ሁሉ ምንጭ የሆነው የዕባቡ ራስ በጎልጎታ መቀጥቀጥና የአዳም ራስ መፈወስ በእግዚአብሔር የብዙ ዘመናት ሐሳብ ስለነበር፥ ኀጢአትን በመሥራትና በማሠራት የደረቀው የዕባቡ ራስ መስቀሉ በቀራንዮ ሲተከል እነክሰዋለሁ ብሎ በአሰበው የክርስቶስ ተረከዝ ላይ ባለው ኀይል አምላካዊ ተቀጥቅጦአል።

ወቅጥቃጤሁሰ ለርእሰ ከይሲ፤ የዕባቡም ራስ መቀጥቀጥ ዳግመኛ እንዳይነሣ፥ እኛም ወደ እርሱ እንዳንመለስ፥ እንደ ሞተ እንድንቆጥረውና እንዳለም እንኳ እንዳናስበው ነው (ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ሰግላዊ)።

ዳግመኛ እንዳይነሣ ሆኖ የተቀጠቀጠውም የአሳቹ ራስ ብቻ ሳይሆን ‹‹በምድር ላይ የኀጥኣንን ራስ (ሥልጣን) እሰብራለሁ›› ተብሎ አስቀድሞ በነቢይ እንደተነገረው፥ በንስሐ የማይመለሱትን፥ በግብር እርሱን የሚመስሉትን የኀጥኣንንም ራስ ጭምር ሰብሮታል (መዝ. 74፥10)። በቀራንዮ የሞትን መውጊያ የተሸከመው፥ የዘንዶው ራስ መቀጥቀጥ እግዚአብሔር ወደ አቀደልን የድል ፍጻሜና ወደሚፈወሰው ራስ በምሥጢር ሠረገላ ይወስደናል።

## የተፈወሰው ራስ፡-

ጽድቁን ጥሎ፥ ቃሉን አቃልሎ ከራሱ ተለይቶ ለነበረው አዳም

የሚበልጠውን ነገር እግዚአብሔር አስቀድሞ አይቶ ነበርና ‹‹አድንህ አለሁ፥ እኔ ፈዋሽህ ነኝ›› የሚለውን የተስፋ ቃል ሰጠው (ዘፍ. 15÷20፤ መጽሐፈ ቀሌምንጦስ)



# “የቦታው ስም ቀራንዮ ነው!”

‹‹እስመ ድውይ ኢይክል ከመ ይግበር ፈውሰ ለርእሱ ወባሕቱ ያስተበቍዖ ለዐቃቤ ሥራይ፤ ታማሚ በተገባለት የተስፋ ቃል መሠረተ ባለ መድኃኒቱ ይፈውሰው ዘንድ ይለምናል እንጂ ለራሱ ፈውስን ማድረግ አይችልምና›› በኀምዘ ከይሲ (በእባቡ መርዝ) የቆሰለው የአዳም የራስ ቅል ዕለተ ፈውስ እስኪደርስ በጎልጎታ ተቀብሮ ፈውሱን ይጠባበቅ ነበር፡፡

እርሱ ብቻ ሳይሆን ልጆቹ ነቢያት በብዙ ትጋት ሆነው ይጠብቁት የነበረው ጊዜ ሲደርስም ‹‹ዐቃቤ ሥራይ መጽአ እምሰማየ ሰማያት ወዕፀ ፈውስ ተረክበ በቤተ ዳዊት፤ የታመመውን ራስ የሚፈውሰው ባለ መድኃኒቱ ከሰማየ ሰማያት መጣ፥ ዕፀ ፈውስም ከዳዊት ቤት ተገኘ፡፡›› (መጽሐፈ ምሥጢር)

ከቤተ ዳዊት የተገኘው ሕሙማን የሚፈለጉት ዐቃቤ ሥራይ ክርስቶስም ለፍጥረቱ ባለው መግቦት የዕባቡን ራስ ቀጥቅጦ የአዳምን ራስ ፈወሰው፡፡ (ኢሳ. 61÷1)

ከሴቲቱ ዘር የተገኘው የፈዋሹ ራስ የአዳምን ራስ የፈወሰው በእርሱ ራስ መመታት ነውና የራስ ቅላችንን ያቆሰለው፥ ልባችንን የሰበረው ኀምዘ ከይሲ (የዕባቡ መርዝ) ተወግዶአል (ዘፍ. 3÷15፤ ኢሳ. 61÷1)፡፡ በመሆኑም የቆሰለው ራስ የተፈወሰበት የቀራንዮ ምሥጢር ድንቅ ነው፡፡ የአዳም ሥጋውና ነፍሱ የተፈወሰባት፣ ድንቅ ምሥጢር የተፈጸመባት “ይቲኬ ቀራንዮ መካነ ተጥሮቱ ወመካነ መቃብሪሁ ለአዳም ወመካነ መስቀሉ ለክርስቶስ…፤ ይህች ቀራንዮ የአዳም የመፈጠሪያው እና የመቃብሩ ቦታ የክርስቶስ የመሰቀያው ስፍራ ናት፡፡ አመ ተሰቀለ ላዕለ ቀራንዮ ወረደ ደም እም ዲበ መስቀሉ ወቦአ ውስተ ምድር ሰጢቆ መቃብሪሁ ለአዳም ለቀድሶተ ነፍሱ ወሥጋሁ…፤ ክርስቶስ በቀራንዮ በተሰቀለ ጊዜ ከመስቀሉ ላይ ደም ወረደ፡፡ የአዳምንም መቃብር ሰንጥቆ ነፍሱንና ሥጋውን ይቀድሰው ዘንድ ወደ ምድር ገባ፡፡ የሚለው የመዳን ምሥጢርና ቦታውም ቀራንዮ (የራስ ቅል) መባሉ አስገራሚ ነው፡፡” (መቃቢስ ዘገዳመ ሐር)

እንደ እንክብል ወርቅ ነጥረው ከወጡት መምህራነ ቤተ ክርስቲያን መካከል አንዱ የሆኑት፥ የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ የነበሩት አለቃ አያሌው ታምሩ ይህን ድንቅ ምሥጢርና ቀራንዮ የራስ ቅል የተባለበትን ትርጉም ሲያብራሩ፦

‹‹የራስ ቅል በሚሉት ቦታ ተሰቀለ የሚለው ትርጉም ከዚያን ቀን ጀምሮ እስከ ዕለተ ምጽዓት ድረስ በምእመናን ጭንቅላት ውስጥ ተሰቅሎ ይኖራል ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት ፍቅሩ፥ መከራው፥ ነገረ መስቀሉ በጭንቅላታችን ተቋጥሮ እንዲኖር ነው፡፡ በዚህ ውስጥ በምእመናን ጭንቅላት እንደተሰቀለ ዘወትር ይኖራል፥ ከዚህ አይወርድም፡፡ ቀራንዮ የእኛ ጭንቅላት ነው፤ እንዳይረሳና እንዳይዘነጋ በጭንቅላታችን ይኖራል፡፡ የእኛ ቀራንዮ የየራሳችን ጭንቅላት ነው›› በሚል ጥልቅ ምሥጢር አመስጥረውታል፡፡

ከቅዱሳት መጻሕፍቱና ከእኒህ ሊቅ ምስክርነት በመነሣት የዕባቡ ራስ ተቀጥቅጦ ርእሰ አዳም የተፈወሰበትን ምሥጢር ባሰብነውና ባነበብነው ቁጥር እንደ ብርሃነ መስቀሉ የሚያበራ እውነት አለው፡፡ በመሆኑም ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር የለምና በፍቅሩ ዐለት ላይ ቆመን ይህን ፍቅር እያሰብን ክብረ መስቀሉን በሕይወታችን ማወጅ ጥሪያችን የሚጠይቀው መንፈሳዊ ግዴታ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል፡፡ (ዮሐ. 15÷13)

ከዚህም ጋር ወደ እርሱ እስክንሄድ ድረስ እንድንኖርባት እግዚአብሔር በሰጠን ሀገር ኑሮን በሰላም መምራት፥ በዓልን በፍቅር ማክበር ዕሤቱ (ጥቅሙ) ለሌላው ብቻ ሳይሆን ለግል ሕይወታችንም ጭምር መሆኑን ‹‹ወሶበ ይሄሉ ሰላም ውስተ ልብየ አሜሃ ተዐርፍ ነፍስየ፤ ሰላም በውስጤ ሲኖር ሰውነቴ ደስ ብሎአት ታርፋለች›› ተብሎ የተጻፈውን ሳንዘነጋ የሚሻለውን መንገድ በመከተል ገባርያነ ሰላም ልንሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም ከራስ የተለየ አካል ሕይወት የለውምና፥ በዚህ የሕይወት አስተምህሮ ጸንተን ከክርስቶስ ጋር በነቀፋውና በመከራው በመተባበር ነገረ መስቀሉን እየሰበክን ለሀገራችንና ለቤተ ክርስቲያናችን የማያጸጽተንን በጎ ሥራ እንድንሠራ ገባሬ ሣህል እግዚአብሔር ይርዳን፡፡

**“ስብሐት ለእግዚአብሔር ለዘሐመ በፈቃዱ÷ ወሞተ በሠምረቱ”**



# የመስቀል በዓል አከባበር ታሪክ በኢትዮጵያ

በረዳት ፕሮፌሰር ቀሲስ ግርማ ባቱ
የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍ ም/ሥራ አስኪያጅ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ መሠረቱን በጠበቀና ባልተለወጠ ክርስቲያናዊ ሥርዐትና ትውፊት ከሚታወቁ ጥቂት አብያተ ክርስቲያን መካከል አንዷ እና ቀዳሚዋ ናት፡፡ ትምህርተ ክርስትና በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አማካይነት ወደ ሀገራችን ከመምጣቱ በፊት የብሉይ ኪዳን ሥርዓትን መሠረት ያደረገ አምልኮተ እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ውስጥ ሲፈጸም መኖሩ፥ ቤተ ክርስቲያን ከጥንታዊነቷ በተጨማሪ የልዩ ገጽታዎች ባለቤት እንድትሆንም አድርጓታል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የቀደምት ቅዱሳን አበው መጻሕፍት፥ ጥንታውያን ትውፊቶችና ባህሎች፥ የበዓላትና የአጽዋማት ሥርዓቶች የሚገኙባት መሆኗ በእጅግ ብዙ የነገረ መለኮትና የታሪክ ሊቃውንት እየተመሰከረላት ያለች የተለየች መንፈሳዊት ዓለም ናት፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአደባባይ ከምታከብራቸው ዓበይት በዓላት መካከል የመስቀል በዓል አንዱ ነው፡፡ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን የተሰቀለበት ቅዱስ መስቀል ለዘመናት ተቀብሮ ከኖረበት ሥፍራ ለማውጣት የመጀመሪያው ሂደት የተጀመረበት የመስከረም 17 በዓል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ድምቀት የሚከበርባቸው ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች አሉ፡፡ እነርሱም፦

- **አንደኛው፦** መስቀል የድኅነታችን መሠረት፥ የአሸናፊነትና የዕርቅ ምልክት፥ የክርስቲያኖች መመኪያ፥ ኀይልና ብርታት በመሆኑ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ" እንዳለ፡፡ (ገላ. 6÷14)
- **ሁለተኛው፦** ደግሞ ይህ ጌታችን የተሰቀለበት መስቀል የቀኝ ክንፍ በተለየ ታሪካዊ አጋጣሚ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣቱ ምክንያት ነው፡፡ ከሁለተኛው ምክንያት ጋር በተያያዘ ይህ ጽሑፍ በተለየ ትኩረት የሚዳስሰው የበዓሉን ታሪካዊ መሠረትና ዕድገት ይሆናል፡፡




## የበዓለ መስቀል ታሪክ

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚመሰክሩት ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፥ ሠላሳ ዓመት ከሦስት ወር በምድር በግልጽ ተመላልሶ፥ እጅግ ብዙ ጸዋትወ መከራን ተቀብሎ፥ ዓለምን ለማዳን በመስቀል ላይ ተሰቀለ። ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ እንዳለ (1ጴጥ. 2÷24)። በመስቀሉ ጥልን ገድሎ፥ የራቀውን ዓለም ወደራሱ በፍቅር ስቦና አቅርቦ ለአዳም ልጆች ሁሉ ሰላምን ዐውጆበታል (ኤፌ. 2÷16)፡ ፡ ቀድሞ የወንጀለኞች መቅጫ የነበረው መስቀል ከዚህ በኋላ የድኅነት ምልክት ሆኖ ተአምራትን ሲያደርግ የቀኑት አይሁድ ዕፀ መስቀሉን ከሰዎች ለመሠወር አስበው ቀበሩት። ከተቀበረበት ተፈልጎ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል ሥፍራው የጥራጊ መጣያ ሆኖ ኖረ።

የመስቀሉ ከተቀበረበት መውጣትና ታሪካዊ እድገቱን ተከትሎ በየደረጃው የመከበሩ ነገር የተያያዘው በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ከታወጀው የክርስትና ሃይማኖት ነጻነት (313 ዓ.ም.) ጋር ነው። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ክርስትናን ከተቀበለ በኋላ መስቀሉ የሚገኝበት ሥፍራ እንዲፈለግና ሲገኝ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራበት ለኢየሩሳሌሙ ጳጳስ መቃርዮስ ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር። በዚሁ መሠረት እናቱ ንግሥት እሌኒ ጌታችን የተሰቀለበትን መስቀል ለማግኘት ፍለጋ አስጀመረች። ቀደም ሲል እንዳነሣነው መስቀሉ የሚገኝበት ቦታ ለዘመናት ጥራጊ የሚጣልበት ሆኖ ስለ ነበር፥ ብዙ ሰዎችን የጠየቀችና ያስጠየቀች ቢሆንም ነገሩን በትክክል የሚያውቅ አልተገኘም። በመጨረሻም ኪራኮስ የተባለ አንድ የአይሁድ ታሪክ ዐዋቂና ሽማግሌ አግኝታ ቅዱስ መስቀሉ የተቀበረበትንና የተጣለበትን አካባቢ ይነግራት ዘንድ ጠየቀችው። ሽማግሌውም፦ "እንጨት አሰብስበሽ ደመራ ሥሪ፥ ሰንድሮስ የሚባል ነጭ ዕጣን አድርጊበትና በእሳት ለኲሺው፥ የዕጣኑ ጢስ ወደላይ ወጥቶ ወደታች ሲመለስ የሚያመለክተውን አቅጣጫ አይተሽ በዚህ ምልክት ታገኚዋለሽ" አላት። እርሷም በነገራት መሠረት እንጨት ደምራ በዚያ ላይም ዕጣን ጨምራ በእሳት ለኮሰችው፤ የዕጣኑ ጢስ ወደ ላይ ወጥቶ ወደ ታች ሲመለስ መስቀሉ ያለበትን ቦታ በጣት ጠቅሶ እንደማሳየት ያህል አመለከተ። ንግሥት ዕሌኒም ጢሱ ያረፈበት ቦታ ቅዱስ መስቀሉ የተቀበረበት እንደሆነ አመነች። ይህ ዕለት መስከረም 17 ሲሆን፤ መስቀሉ የሚገኝበት ሥፍራ የታወቀበት

ቁፋሮ የተጀመረበት በመሆኑ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ድምቀት ይከበራል፡፡

በምልክቱ መሠረት መስከረም አሥራ ሰባት የተጀመረው ቁፋሮ ለወራት ከተካሄደ በኋላ በመጋቢት 10 ላይ ሦስት መስቀሎች የጌታችንና በግራና በቀኝ የተሰቀሉት የሁለቱ ወንበዴዎች ተገኙ፡፡ ከሦስቱ መስቀሎች የጌታችን የሆነውን መለየት ደግሞ ቀጣዩ ጉዳይ ነበርና ሕሙማንና ሙታንን እንዲሁም ሌሎች ፈውስ ፈላጊዎች ጋር በማገናኘት ሦስቱንም መስቀሎች ሞከሯቸው፡፡ የጌታችን መስቀል ተአምራትን በማድረግ ብቸኛ ሆኖ ሊታወቅ ቻለ፡፡

## የቅዱስ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት

ከቅዱስ መስቀሉ ክፍሎች የተወሰዱና የተለያየ መጠን ያላቸው ግማዳተ መስቀል በበርካታ የዓለማችን ክፍሎች ይገኛሉ ተብሎ ይነገራል፡፡ ከእነዚህ መካከል ካቶሊኮች በሮም፥ በፓሪስ፥ በኢየሩሳሌም፥ በስፔንና በሌሎችም ቦታዎች እንደሚገኝ የሚናገሩት አንዱ ነው፡፡ ምሥራቃውያን ኦርቶዶክሶችም በበኩላቸው በግሪክ አቶስ ተራራ ላይ ስለሚገኘው ግማደ መስቀል በቆጵሮስና በዩክሬን ስለሚገኙ የመስቀሉ ክፍሎች የሚተርኩት ታሪክ አላቸው፡፡ አኃት ወይም ኦሪየንታል ከምንላቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል ደግሞ የአርሜንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና የግብጽ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከመስቀሉ በዓል አከባበር በተያያዘ በእነርሱ ዘንድ ስለሚገኙ ክፍሎች የሚናገሩባቸው ታሪኮች አሏቸው፡፡

ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም (350-386 ዓ.ም.) እንደተናገረው የመስቀሉ ክፍሎች በመላው ዓለም ተሠራጭተዋል፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ የዓለም ነገሥታት መስቀሉ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ለራሳቸው ለመውሰድ ይጣሉበት እንደነበርና በዘመኑ የነበሩ የሃይማኖት አባቶች መስቀሉን ከአራት ክፍል በመክፈል በስምምነት እንዳከፋፈሏቸው የሚናገር ታሪክ አለ፡፡ በዚህ ጊዜ በአፍሪካ ስም የተከፈለውን የመስቀሉን የቀኝ ክንፍ የግብጹ ፓትርያርክ ተረክቦ ከሌሎች ንዋየ ቅድሳት ጋር በክብር አስቀመጠው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በ2006 ዓ.ም ተተርጉሞ የታተመው መጽሐፈ ጤፉት በመግቢያው እንዳሰፈረው “በ614 ዓ.ም የፋርስ ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ወረረ፥ ብዙ ጥፋትም አደረሰ፥ መስቀሉንም ማርኮ ወደ ፋርስ ወሰደው፡፡ በ627 ዓ.ም. ክርስቲያኑ የሮም ንጉሥ ሕርቃል በክርስቲያኖች ጥያቄ ፋርስን ወግቶ መስቀሉን ወደ ኢየሩሳሌም መለሰው፡፡ ቆይቶም ኢየሩሳሌም በዓረቦች እጅ ስትወድቅ ክርስቲያኖች መስቀሉን ደበቁት፡፡ ቢሆንም በተለያዩ ተጽዕኖዎች ምክንያት ደብቀው ማቆየት አልቻሉምና ወደ እስክንድርያ አመጡት፡፡ ከእስክንድርያም ... በእግዚአብሔር ፈቃድና በነገሥታቱ ጥረት ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ መጣ፡፡”



ዕውቁ የታሪክ ጸሓፊ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ስለ ዐፄ ዳዊት የሚናገረው ያገራችን ታሪክ ብለው ያነሡት ሐሳብ የዚሁ ታሪክ አካል ተደርጎ ይተረካል፡፡ ይኸውም፦ «ዳዊት ካልእ ወልዱ ለሰይፈ አርዕድ ነግሠ ፳ወ፱ ዓመተ፡፡ ወበመዋዕሊሁ መጽአ ዕፀ መስቀሉ ለክርስቶስ ወገብረ ፍሥሓ ...» እያለ የሚቀጥለውን ታሪክ የያዘ ነው፡፡ ይህም የዐፄ ሰይፈ አርዕድ ልጅ ዐፄ ዳዊት 29 ዓመት መንገሡን፥ በዘመነ መንግሥቱ ግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱን የሚተርክ ነው፡፡ የግብጽ መሪዎች ክርስቲያኖችን በሃይማኖታቸው ምክንያት በግብርና በቀረጥ ሰበብ እያደረጉ ሲያስጨንቋቸው፥ ሊቀ ጳጳሱን አባ ሚካኤልንም ባሠሯቸው ጊዜ ዐፄ ሰይፈ አርዕድ ክርስቲያኖቹን ለመታደግ ዘምተው ነበር፡፡ “ወሶበ ሰምዐ ንጉሠ ኢትዮጵያ ሰይፈ አርዕድ ከመ ኰነንዎ መኳንንተ ተንባላት ለዝንቱ አብ ሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤል ወሞቅሕዎ፡፡ ቀንዐ ቅንዐተ መንፈሳዊተ በእንተ ዘኮነ እስክንድርያ ወኢትዮጵያ አሐተ ሃይማኖተ፡፡ ወወረደ ብሔረ ግብፅ ዘምስለ ብዙኅ ሠራዊት፡፡” ታሪከ ነገሥት በዚህ ታሪክ ስምምነት ያለው ሲሆን፤ ልዩነቱ የሊቀ ጳጳሱን ስም አባ ማርቆስ ማለቱ ላይ ብቻ ነው፡፡

ዐፄ ሰይፈ አርዕድ ግብጽ ወርደው ጳጳሱን አስፈትተው፥ ክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው መከራ እንዲቆም አዝዘው ተመለሱ፡፡ ዐፄ ሰይፈ አርዕድ 28 ዓመት ገዝተው ዐረፉ፡፡ ዕረፍታቸውን የሰማው የግብጽ መሪ ጳጳሱን በድጋሚ አሰራቸው፥ ክርስቲያኖችንም ማሰቃየት ጀመረ፡፡ ይህን የሰሙት ዐፄ ዳዊት ዳግመኛ ወደ

ግብጽ ዘመቱ። በመንገዳቸውም የዓባይን ወንዝ ውኃ የፍሰት አቅጣጫውን አስቀይረው ወደ በረሃ እንዲፈስ አስደረጉት። ይህን የሰማው የግብጹ መሪ ጳጳሱንም ሆነ ሌሎች እስረኞችን ከእስር ለቀቃቸው። እጅ መንሻ የሚሆን ብዙ ወርቅ በመላክ ጭምር ዐፄ ዳዊት ዘመቻቸውን ትተው እንዲመለሱ ቢያስለምናቸውም አገዛዙን እንዲያስተካክል ከመጠየቅ በተጨማሪ መስቀሉን ስጠኝ ብለው አስጨነቁት። ይህ ካልሆነ በቀር እንደማይመለሱ የገባው የግብጹ መሪ፦ መስቀሉን፥ ሉቃስ የሣላቸውን ሥዕላት፥ ወንጌላዊው ዮሐንስ የሣለውን ሥዕለ ስቅለት ጨምሮ ለንጉሥ ዳዊት ላከ። ይህ የተፈጸመው መስከረም 10 ቀን ነው። ንጉሡም በዚህ ቀን ታላቅ በዓል አደረገ። ስሙንም የዐፄ መስቀል በዓል ብለው ሰየሙት። እንዲሁም ከመስከረም 17 ጀምሮ ለ7 ቀናት ታላቅ በዓል ተደረገ። ከዚህ በኋላም፥ እነዚህን ቅዱሳት ንዋያት በመያዝ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ላይ ሳሉ፥ ስናር የተባለ ቦታ ላይ ዐፄ ዳዊት በድንገት አረፉ። እንደ መጽሐፈ ጤፉት ትረካ ንጉሡ ሲሞቱ ቅዱሳት ንዋያቱ እዚያው ስናር እንዲቆዩ ግዴታ ሆነ፤ እናም በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ሊገቡ ቻሉ።

በሌላ የታሪክ መንገድ ደግሞ ዐፄ ሰይፈ አርዕድ ለጦርነት በተዘጋጁ ጊዜ የእስክንድርያው ፓትርያርክ በመካከል ገብተው ለመሸምገል መልእክተኛ ላኩ። የኢየሩሳሌሙ ፓትርያርክ ዮሐንስም በጉዳዩ ስለገቡበት የመልእክተኞቹ መሪ ሆኑ። ከረጅም ጊዜ በኋላ ኢትዮጵያ ሲደርሱ ዐፄ ሰይፈ አርዕድም ዐፄ ንዋየ ማርያምም ዐርፈው በዙፋን የነበሩት ንጉሥ ዐፄ ዳዊት ነበሩ። ንጉሡ መልእክተኞቹን አክሱም ድረስ ሄዶ ተቀበላቸው። በመካከላቸው ስለሚኖር ግንኙነትም ተወያዩ፤ የክርስቲያኖች መከራ የሚቀምበት ጥያቄያቸውም ተቀባይነት አገኘ። የኢትዮጵያ ሰዎች ያለ ችግር ወደ ግብጽና ኢየሩሳሌም የሚሄዱበት ዕድልም ተገኘ። በዚህ የተበረታቱት ዐፄ ዳዊት የመስቀሉ ግማድ እንዲላክላቸው ወደ ኢየሩሳሌም መልእክት ላኩ። ከላይ የተጠቀሱት መስቀሉ፥ ቅዱሳት ሥዕላትና ሌሎች ንዋያት ተልከውላቸው ሊቀበሉ በወጡበት ስናር ላይ እንደ ሞቱ ይነገራል። በዚህኛው ታሪክ ውስጥ መስቀሉ ከግብጽ ሳይሆን ከኢየሩሳሌም መምጣቱ እንደሚነገር ማስተዋል ይቻላል። ነገር ግን በሌሎች በርካታ የታሪክ ምንጮች ከዚህ ዘመን በፊትም በኢየሩሳሌም የነበረውን መስቀል የዓለም ሀገራት እንደተከፋፈሉት ስለሚነገር በመጽሐፈ ጤፉት የሚገኘው የተሸለ የታሪክ መንገድ ሆኖ ይገኛል። በዚህ መሠረት ዐፄ ዳዊት ስናር ላይ ስላረፉ፥ መስቀሉን ከስናር ተቀብለው ወደ ኢትዮጵያ ያመጡት ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ናቸው። በ1443 ዓ.ም. ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከነበረበት ቦታ በማስመጣት በ1446 ዓ.ም. መስከረም 21 ቀን አምባሰል፥ ደብረ ነገሥት (ደብረ ከርቤ ብለው የሰየሚት ቦታ) ደርሷል። ንጉሡም አብሮ በመሄድ፥ ቤተ ክርስቲያኑንም አሳንጿል።

ዐፄ ዳዊት ከመሞታቸው በፊት መስቀሌ በመስቀል ላይ ይቀመጣል የሚል ራእይን አይተው ነበር። ይህንኑ ራእይ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብም “መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ አኑር” ሲላቸው አይተዋል። ይህን ቦታ ለማግኘትም ለሦስት ዓመታት ደክመዋል። ከሦስት ዓመት በኋላ አምባሰል (የአሁኗ ደብረ ከርቤ) ሲደርሱ በመልአኩ በቅዱስ ዑራኤል ባገኙት ማረጋገጫ መስቀሉን አሳርፈዋል።

በተለያየ መንገድ በሚተረከው ታሪክ ውስጥ ያለው ዋና ጉዳያችን የቅዱስ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንም እንደዚሁ የግማደ መስቀሉን ወደ ሀገራችን መምጣት አስረግጣ ትናገራለች። በዓሉንም በመግቢያችን በጠቀስናቸው ሁለት መሠረታዊ ሐሳቦች መነሻ በድምቀት ታከብረዋለች። በቅዱስ ያሬድ ቃል መስቀል ብርሃን ለኵሉ ዓለም መሠረተ ቤተ ክርስቲያን እያለች በመስቀል ያዳነንን አምላክ ታመሰግንበታለች። “በመስቀሉ አርኃወ ገነተ፥ በመስቀሉ ገብረ መድኀኒተ፥ መስቀል ቤዛነ፥ መስቀል መድኀኒትነ ለእለ አመነ መስቀልከ መርሐ ይኩነነ” እያለች ምስጋናን ከተማኅፅኖ ጋር ታቀርብበታለች። ምእመናን በክርስቶስ አምነው በመስቀሉ አማትበው አጋንንትን፥ መናፍቃንን፥ ፍትወታት እኩያትን ድል ሲያደርጉ ይኖራሉ። ከዚህ የተነሣ በተለይ በሀገራችን ኢትዮጵያ ኪነ ጥበቡ፥ በመጻሕፍቱ፥ በቅዱሳት ሥዕላቱ፥ በቤታቸው፥ በልብሳቸው ሁሉ ምልክቱን ያደርጉታል። በሃይማኖት ሕይወታቸው ከሚጠብቁት የመስቀሉ ክብር ጋር በተያያዘ በዓለ መስቀል ለብዙ ክፍለ ዘመናት ሲከበር ኖሯል፥ አሁንም እየተከበረ ይገኛል። ቤተ ክርስቲያን በበዓሉ ሰላምን ታውጃለች፥ ፍቅርን ትሰብካለች፥ በመስቀል የተፈጸመውን ሁሉ ትዘክርበታለች። ከዚህ የተነሣ የበዓለ መስቀል ፋይዳ እጅግ ከፍ ያለ ነው።

## የመስቀሉ ኀይልና በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን!



# ነገረ መስቀል ከመንበረ ጸባዖት እስከ ቀራንዮ

በሊቀ ሥዩማን ግርማ ቤጊ
የሊቃውን ጉባኤ አባል

የነገረ መስቀል ጉዳይ ሲነሣ ትዝ የሚለንና ልንረሳው የማይገባ፥ የሰው ፍቅር አገብሮት ከልዑል ዙፋኑ ወርዶ በማይለወጥ ፍቅሩ እስከ ሞት የወደደን የቀራንዮ በግ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በመልዕልተ መስቀል ላይ ተሰቅሎ ተመን የማይገኝለትና በቃላት ሊገለጥ የማይችል የደም ካሳና የማዳን ሥራው ነው፡፡ የነገረ መስቀሉን ታላቅነት ሊቃውንት ሲገልጹ፦ 'አዳም ከተፈጠረበት ጥበብ ይልቅ የዳነበት ጥበብ ይበልጣል' በማለት ያመሠጥራሉ፡፡ በመሆኑ መስቀልንና የክርስቶስን የማዳን ሥራ ለያይቶ መናገር አይቻልም፡፡

ከዐበይት ነቢያት አንዱ የሆነው ነቢዩ ኢሳይያስ፦ "ውእቱ ነሥአ ደዌነ ወጾረ ሕማመነ ወበእንቲኣነ ሐመ ወንሕነሂ ርኢናሁ ሕሙመ ወቅሡፈ በሕማም፡፡ ወውእቱሰ ቄስለ በእንተ ኀጢአትነ ወሐመ በእንተ ጌጋይነ ትእምርተ ሰላምነ ወበቍስለ ዚኣሁ ሐየውነ ቍስለነ፤ በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፥ ሕማማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደተቀሠፈ እንደተቸገረም ቈጠርነው፡፡ እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ተሰለ፥ ስለ በደላችን ደቀቀ፥ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበር፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን" ሲል ስለ ነገረ መስቀሉ አስቀድሞ በትንቢቱ ጽፎልናል፡፡ (ኢሳ. 53÷4፡5)

መስቀል ማለት በአራቱም መዓዝን የተመሳቀለ ወይም የተዘረጋ ማለት እንደሆነ የቋንቋ ምሁራን ይናገራሉ፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የነገረ መስቀል ትርጉም በሦስት ይከፈላል፦

1ኛ) የዓለም መድኀኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች ሲል የተቀበለው መከራ፤

2ኛ) ጻድቃን ሰማዕታት ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስን በማመናቸው የሚቀበሉት መከራ መስቀል፤

3ኛ) ኢየሱስ ክርስቶስ ለድኅነተ ዓለም ሲል የተሰቀለበት ቅዱስ ዕፀ መስቀል ናቸው፡፡

በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣው ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ስለ ነገረ ቅዱስ መስቀል አስቀድሞ በድጓው ያመሠጠረውን፥ በኋላ የተነሣው አባ ጽጌ ድንግልም በማኅሌተ ጽጌ ድርሰቱ ስለ ነገረ መስቀሉ፦ "ዝንቱ መስቀል መንበረ ነበልባል ዘኪሩቤል ቢጽ አምሳለ ስምኪ ድንግል ርቡዐ ሆህያት ወገጽ፤ ይህ ቅዱስ መስቀል በዘባነ ኪሩቤል ለዘላለም ጸንቶ የሚኖረው የሥላሴ መንበር ምሳሌ ነው፤ ወይም መንበረ ልዑልን ይመስላል" በማለት ከገለጸ በኋላ፤ ምሥጢሩን ከነገረ ሥጋዌ ጋር በማያያዝ፦ "አምሳለ ስምኪ ድንግል ርቡዐ ሆህያት ወገጽ፤ ድንግል ማርያም ሆይ፥ ይህ ቅዱስ መስቀል በስምሽ ምሳሌ አራት ፊደላትና አራት ገጽ ነው" በማለት የድንግል ማርያምን ስምና የሥላሴን ዙፋን በማነጻጸርና በማመሳሰል ተርጉሞታል፡፡

ከዚህ ከአባ ጽጌ ድንግል አገላለጽ የምንረዳው የመስቀልና የመንበረ ልዑል፥ የኪሩቤልና የድንግል ማርያም ስሞች ፊደላት በቊጥራቸውና በክብራቸው ተመሳሳይ መሆናቸውን ነው፡፡ ይኸውም መስቀልን ከመንበረ ጸባዖት፥ መንበረ ጸባዖትን ከመስቀል፤ ማሕፀነ ድንግልን ከጽርሐ አርያም፥ ጽርሐ አርያምን ከማሕፀነ ድንግል ማርያም ጋር በማመሳሰል ጽፎልናል፡፡ ይህ ቃል እኛንም በዐይነ ሕሊናችን ሰማየ ሰማያትን አልፈን፥ በጽርሐ አርያም የሥላሴን አኗኗር እንድንመረምር የሚያነሳሣ ነው፡፡

ሊቁ ቅዱስ ያሬድም በመንበረ ጸባዖት በአብ እሪና የነበረና ያለ አካላዊው ቃል ክርስቶስ፥ በተለየ አካሉ ከልዑል ዙፋኑ ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፥ በማእከለ ምድር ቀራንዮ መስቀልን ዙፋኑ አድርጎ ዓለምን ማዳኑን ሲገልጽ፦ “ዘወረደ እምላዕሉ አይሁድ ሰቀሉ ወሚመ ኢያእመሩ እግዚአ ኵሉ ዘያሐየ በቃሉ” በማለት ከላይ ከሰማይ የወረደውን አካላዊውን ቃል ክርስቶስን አይሁድ ፈጽሞ አላወቁትም፥ በቃሉ ሕሙማንን የሚያድነውን የሁሉን አምላክ ክርስቶስን ሰቀሉት ሲል ክርስቶስን ከነገረ መስቀሉ ጋር አያይዞ ተናገረ፡፡ (ጾመ ድጓ ዘመስቀል)

በመሆኑም የቅዱስ መስቀል በቀራንዮ መተከልና የወልደ እግዚአብሔር ሞት በአይሁድ ጥላቻና ክፋት የተቀነባበረ ሴራ ብቻ ሳይሆን ጥበበ እግዚአብሔር ያለበት መሆኑን ነው የምንረዳው፡፡ ፈጣሬ ዓለማትና አምጻኤ ዓለማት ቅዱስ እግዚአብሔር ይህንን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ከመፍጠሩ አስቀድሞ ዙፋኑን በዘባነ ኪሩቤል ላይ ሲዘረጋ፥ በአራቱ ማዕዘነ ዓለም በአምሳለ መስቀል መፍጠሩ የነገረ መስቀልን ምሥጢራዊ አመጣጥንም ያሳያል፡፡

## ነገረ መስቀል በኪሩቤልና በድንግል ማርያም፤

«ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል ወትፌደፍድ እምሱራፌል፤ ክብርሽ ከኪሩቤልና ከሱራፌል ይበልጣል» ተብሎ የተነገረላት ቅድስት ድንግል ማርያም፤ ኪሩቤል የሥላሴን ዙፋን የሚሸከሙት በጸጋው ሲሆን፤ ድንግል ማርያም ግን ሰማይና ምድር የማይችሉት እሳተ መለኮትን ዘጠኝ ወር ከአምስት ወር በማሕፀንዋ በመሸከምዋ ለአካላዊው ቃል ለወልድ ዙፋኑ ሆናለች፡፡

ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው፦ “ኦ ድንግል ሶበ ኀደረ ውስተ ከርሥኪ እሳተ መለኮት እፎኑ ኢያውዐየኪ፤ ድንግል ሆይ፥ እሳተ መለኮት በማሕፀንሽ በአደረ ጊዜ እንደምን አላቃጠለሽም?» ሲል፥ የድንግል ማርያም ጸጋ ልዩ በመሆኑ ክብሯም ከኪሩቤል የሚበልጥ መሆኑን እንረዳለን፡፡

## መስቀል በነቢዩ ሕዝቅኤል ራእይ፤

ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በአምስተኛው መቶ ዓመተ ዓለም አካባቢ የነበረው ራእየ ኀቡአት ነቢዩ ሕዝቅኤል ሕዝበ እስራኤልና ሕዝበ ይሁዳ በፈጸሙት ተደጋጋሚ በደል ምክንያት ተማርከው ወደ ባቢሎን በወረዱ ጊዜ መከራውና ሥቃዩ ስለጸናባቸው፥ ባለ ራእዩ ሕዝቅኤል እግዚአብሔር ለሕዝቡ የመከራውንና የሥቃዩን ዘመን እንዲያሳጥርላቸው በፈለገ ኮቦር በሰፊሐ እድ፥ በአንቃእድዎ ሕሊና ሆኖ ሲጸልይ ምሥጢራት ተገልጾለት እግዚአብሔርን በዘባነ ኪሩቤል ተቀምጦ አየ፡፡

የእግዚአብሔርን ዙፋን የሚሸከሙት ኪሩቤልም በብርሃን የተሞሉ አራት አራት ዐይንና አራት አራት ገጽ ያላቸው ሆነው፥ ክንፎቻቸውንም በአምሳለ መስቀል በአራቱ አቅጣጫ መዓዝነ ዓለም በምሥራቅ፥ በምዕራብ፥ በሰሜንና በደቡብ አቅጣጫ ዘርግተው አይቶ በመደነቅ፥ የእግዚአብሔርንም ሥራ በአንክሮ ሲገልጽ፦ “ከመ ርእየተ እለ ቄጥሩ ገጸ በገጽ ኢይትጸገሩ ኀበ አንጸረ ቀዳማዊ የሐውሩ እንዘ ኢየአርፉ ይሴብሑ እሉ እሙንቱ ገጸ ሰብእ ወገጸ እንስሳ፥ እሉ እሙንቱ ገጸ ንስር ወገጸ አንበሳ” ሲል ተናገረ፡፡

እነዚያ እለቄጥሩን (ጉባኤ መላእክት) በአራቱም መዓዝነ ዓለም አቅጣጫ ክንፎቻቸውን በአርኣያ መስቀል መዘርጋታቸው፡- ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድን ሰው ሁነህ፥ ሥጋ ለብሰህ እንዲህ ባለ መስቀል ተሰቅለህ ዓለምን ታድናለህ ሲሉ ወይም በደመ መስቀሉ ዓለምን የሚያድን መሆኑን የሚያሳይ ትንቢታዊ ራእይ ነው፡፡ (ሕዝ. 1፥1-12 ትርጓሜ፤)

በመቀጠልም ገጸ ሰብእ ወይም የሰው መልክ ያለው መልአክ በገጹ በጌታችን ይመሰላል፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ በመስቀል ላይ ሥጋውን ርሶ ደሙን አፍስሶ ያደረገውን የማዳን ሥራንና ነገረ መስቀሉን የሚያመለክት ስለሆነ ነው፡፡ ገጸ አንበሳ ወይም የአንበሳ መልክ ያለው መልአክ በገጹ የይሁዳ

አንበሳ የተባለው ክርስቶስ ሲሆን፤ በመስቀል ሞትን ድል አድርጎ በገዛ ሥልጣኑ መነሣቱን የሚያመለክት ነው። ገጸ ንስር ወይም የንስር መልክ ያለው መልአክ ክርስቶስ ወደ ባሕርይ አባቱ በክብር ማረጉን /የነገረ ዕርገቱ/ አመልካች እንደሆነ ይተረጉማሉ። (ሕዝ. 1÷4-9፤ ራእ. 1÷28፤ 4÷6፡7፤ መቅ.ወን. 2ኛ ጉባኤ)

የሕዝቅኤል ራእይ ትእምርተ ድኅነት የመስቀል ምሳሌ ነው። ይኸውም እግዚአብሔር፦ ይህን ዓለም በአራት ገጽ፥ ኪሩቤልን በአራት ገጽ፥ ገነትን በአራት ገጽ ሲፈጥር ዓለምን በመስቀል አምሳል አብሮ መፍጠሩን እንረዳለንና።

## መስቀል የአራቱ መዓዝነ ዓለም ምሳሌነት፤

ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ይህ ዓለም ሲፈጥር በአራት አቅጣጫ ዘርግቶ የፈጠረው በክርስቶስ መስቀል አምሳል ነው። ምክንያቱም የመስቀል ቅርጽ የሰውን ቅርጽ ይመስላልና። የኢየሱስ ክርስቶስ በማእከለ ምድር ቀራንዮ መሰቀል በአራቱም መዓዝነ ዓለም ያሉትን የአዳም ልጆችን ሁሉ በደመ መስቀሉ ማዳኑን የሚያመለክት ነው፤ "... ወገብረ መድኀኒተ በማእከለ ምድር" እንዲል። (መዝ. 73÷12፤ ራእ. 7÷1)

## ቅዱስ መስቀል በማኅበረ መላእክት፤

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ የተባለው ሊቀ የሥነ ፍጥረትን ታሪክ በጻፈው አክሲማሮስ በተባለው መጽሐፉ ዲያብሎስ በትዕቢቱ ፈጣሪውን ክዶ ራሱ ፈጣሪ ነኝ በማለት፥ መላእክትን የፈጠርኋችሁ እኔ ነኝ በማለት ስቶ ለማሳትና ክዶ ለማስካድ በነዛው የሐሰት ንግግር በቅዱሳን መላእክትና በዲያብሎስ መካከል ጦርነት እንደተጀመረ ይገልጻል።

በዚህም መነሻ "የሚካኤል ሠራዊት በሃይማኖትና በአንድነት ጸንተው ከዲያብሎስ ጋር ሲዋጉ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሸነፉና "ፈቃድህ ባይሆን ነው" ብለው እግዚአብሔርን ጠየቁ። እግዚአብሔርም «ፈቃዴስ አይደለም፤ ድል የምትነሡበትን ኀይል እንድታውቁ ብየ ነው እንጂ» ብሎ ለቅዱሳን መላእክት በየክንፋቸው ላይ የብርሃን ትእምርተ መስቀል ቀረጸባቸው። ከዚያ በኋላ ሂደው ሲገጥሙት በብርሃን ትእምርተ መስቀል ምልክት ዲያብሎስን ድል አድርገውታል (መዝ. 59÷4)። "ወሞእዎ እሙንቱ በእንተ ደመ በግዑ፤ የሰጣቸው የብርሃን ትእምርተ መስቀል የእግዚአብሔር በግ ደም ምልክት የተሳለበት የብርሃን መስቀል ምልክት ነው።" ይህም የሚያሳው መስቀል የጠላት ድል መንሻ ምልክት መሆኑን ነው። (መቅድመ ወንጌል፤ ራእ. 12÷7፤ ትርጓሜ)

ነቢዩ ኢሳይያስ በምዕ. 14 ቊ. 12 ላይ የዲያብሎስን በቅዱሳን መላእክት ተሸንፎ መውደቅ ሲገልጽ፦ "አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ? አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፥ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተ፣ረጥህ? አንተም በልብህ፦ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፥ በሰሜንም ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፥ ከደመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፥ በልዑልም እመሰላለሁ አልህ፤ ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጕድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ" ሲል እንደገለጠው፤ ቀድሞ በመላእክት ትእምርተ መስቀል ምልክት ድል የተመታው ዲያብሎስ በኋላም በክርስቶስ ደመ መስቀል ድል መሆኑን ያረጋግጣል።

ያ በብርሃን መስቀል የተመታ ጠላት ዲያብሎስ "ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ዲያድሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድርም ተጣለ፤ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ" ሲል ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ ገልጿል። መላእክትም ዲያብሎስ እሑድ ከኢየሩሳሌም ሰማያዊ ወደ ኢዮር እንዳወረዱት፤ ረቡዕ ደግሞ ወደዚህ ዓለም፥ ሐሙስ ግን ወደ እንጦርጦስ አውርደው እንደጣሉት ተጽፎአል (ራእ. 12÷7-9)። የቅዱሳን መላእክት ሥዕል በብርሃን ትእምርተ መስቀል የሚሳለው በዚህ ትውፊት መሠረት እንደሆነ ሊቃውንት ይናገራሉ። «አስተርአያ በክብር ጸዋሬ ዜና ገብርኤል ውስተ እዴሁ በትር ዘከተማሁ መስቀል -- መልካም የምሥራች የተሸከመና በእጁ በትረ መስቀል የያዘ ገብርኤል በክብር ታያት ወይም ተገለጸላት፤» እንዳለ ቅዱስ ያሬድ። (ሉቃ. 1÷26፤ ራእ. 12÷17)

## መስቀል ዕፀ ሕይወት ወዕፀ መድኀኒት፤

ቅዱስ ያሬድ ወደ ጥንተ ፍጥረት ሂዶ፦ "ወተከለ 3ተ ዕፀ ሕይወት በዲበ ምድር" እንዳለ፥ እግዚአብሔር በገነት ውስጥ የፈጠራቸው ዕፀዋት ሦስት ናቸው አለ። ከሦስቱ ዕፀዋት አንዱ ዕፀ ሕይወት ነው፤ "አዳምም ዕፀ በለስን ባይበላ ሺህ ዓመት ኑሮ ዕፀ ሕይወትን በልቶ፥ ታድሶ

መንግሥተ ሰማያት ይገባ ነበር"፤ ውዳሴ ማርያም ዘሐሙስ ትርጓሜ፤ እንዲሁም፡- «... መድኀኒት ዕፀ ሕይወት ዝንቱ ውእቱ መስቀል. ...» በማለት መስቀልን ዕፀ ሕይወት ብሎ ተርጉሞታል፡፡ የገነት አቀማመጥም በአራት መዓዝን በመስቀል ቅርጽ እንደሆነ ገልጻ*ል፡፡ (ቀሌምንጦስ ገጽ 5)

## የመስቀል ምሳሌ በብሉይ ኪዳን ዘመን፤

### የኖኅ መርከብና መስቀል፤

ድኅነተ ሥጋ ለድኅነተ ነፍስ ምልክት ነውና የብሉይ ኪዳን መዳን ለሐዲስ ኪዳን መዳን ምልክት ነው፡፡ የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ሲነገር መንስኤው የሰው ልጆች በደልና ኀጢአት ሲሆን መደምደሚያውና መዳረሻው ደግሞ በቀራንዮ በመስቀል ላይ የፈሰሰው የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ደም ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የሰው ልጅ በምድር ላይ እየበዛና ትውልዱም እየሰፋ በሄደ ቁጥር የሰው ኀጢአትና በደልም አብሮ እየበዛና እየጨረ በመሄዱ በእግዚአብሔርና በሰው ልጆች መካከል የነበረው ፍቅር እየደበዘዘና ልዩነት እየሰፋ መምጣቱ ይታወቃል ነው፡፡

እግዚአብሔር ወዳጆቹን ከክፉዎች መካከል መርጦ ለማዳን ችግር ስለሌለበት አቤልን ከቃየል እንደለየ፥ በሰብአ ትካት ጊዜ ከሰው በደል የተነሣ ምድር በእግዚአብሔር ፊት ስለተበላሸች እግዚአብሔር ምድርን በንፍር ውኃ ለማጥፋት ወሰነ፡፡ ነገር ግን ቸርነቱ ብዙ ስለሆነ የሰውን ዘር ጨርሶ ለመደምሰስ ስላልፈለገ በዚያን ጊዜ ከነበሩት ሰዎች የተሻለ አመለካከትና ቅድስናን ይዞ የተገኘውን ኖኅንና ጥቂት ቤተሰቦቹን ለማዳን ሲል “ግብር ታቦተ በዘትድኅን” አለው፡፡ ኖኅም መርከቡን ሠርቶ ራሱን፥ ቤተሰቦቹንና ሌሎች ፍጥረታትን ከማየ ድምሳሴ ማዳኑን በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ እናገኛለን፡፡ (ዘፍ. 6÷8፤ ኢሳ. 1÷9)

እጅግ የሚገርመውና የሚያስደንቀው ነገር የእግዚአብሔር ቅጣት እንደ ሰው ልጅ ኀጢአት ብዛትና ክፋት ሳይሆን የእግዚአብሔር ትዕግሥቱና የምሕረቱ ብዛት ያስደንቃል፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር 130÷3 “እመሰ ኀጢአተነ ትትዐቀብ እግዚኦ እግዚኦ መኑ ይቀውም፤ አቤቱ ኀጢአትንስ ብትጠባበቅ በፊትህ ማን ይቆማል?» እንዳለ፤ ምሳሌውም ኖኅ መርከብ የሠራበት እንጨት ምሳሌውና ፍጻሜው ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ዕፀ መስቀል ምሳሌ መሆኑን ቅዱስ ጴጥሮስ፦ “ዐይ ይእቲ ዛቲ መድኀኒት እንተ ኀሠሥዋ፥ወያድዋ ነቢያት፥ ወይቤሎ ለኖኅ አመ አይኅ ግበር ታቦተ በዘትድኅን፥ እትአመን ባቲ እስመ አርዓያ መስቀል ይእቲ” በማለት የኖኅ መርከብ የመስቀል ምሳሌ መሆኑን ጽፎልናል፡፡ (1ጴጥ. 3÷20፤ ዕብ. 11÷7)

### ዕፀ ሳቤቅና ዕፀ መስቀል፤

አበ ብዙኃን የተባለው አብርሃም በዘመኑ ከነበሩ ሰዎች ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ ፍጹም ሃይማኖተኛ ሰው እንደ ነበረ መጻሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ እግዚአብሔርም የአብርሃምን ሃይማኖት ለዓለም ሊገልጥ ፈልጎ አብርሃምን፦ “አንድ ልጅህ ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞርያ ምድር ሂድ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ ታራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለው” (ዘፍ. 22÷1-19)

ዐርከ እግዚአብሔር አብርሃምም በማለዳ ተነሥቶ ልጁ ይስሐቅን በአምሳለ ክርስቶስ እንጨቱን አሸክሞ ወደ ተራራ ጉዞ ጀመሩ፡፡ አረጋዊው አብርሃምም በሦስተኛው ቀን እግዚአብሔር ወደ አሳየው ተራራ ሲደርስ የመሠዊያውን እንጨት ከረበረበ በኋላ፥ ዐይኑን ወደ ላይ አንሥቶ እጁን በይስሐቅ ላይ ሲዘረጋ፥ የእግዚአብሔር ድምፅ ከሰማይ ጠራና፡ «አብርሃም አብርሃም በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ! አንድ ልጅህን አልከለከልህምና፥ እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደሆንህ ዐውቄአለሁና» ሲል ከለከለውና ቤዛ ይስሐቅ የሆነውንና ቀንዱ በዕፀ ሳቤቅ የታሰረ ነጭ በግ አውርዶለት በይስሐቅ ፈንታ ሠዋው፡፡ ይህንንም ሊቁ ቅዱስ ያሬድ “አብርሃም ወሰዶ ለይስሐቅ ወልዱ ከመ ይሡዖ፥ አውረደ ሎቱ ቤዛሁ በግዐ እትነዝ አቅርንቲሁ በዕፀ ሳቤቅ፥ ዕፀ ሳቤቅ ብሂል ዕፀ ሥርየት መስቀል” በማለት ዕፀ ሳቤቅን ከነገረ መስቀሉ ጋር አገናኝቶ ጽፎአል፡፡ (ቅዱስ ያሬድ)

ፍጻሜና ምሳሌው፦ አብርሃም የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ፥ ይስሐቅ የዚህ ዓለም ምሳሌ፥ ቤዛ ይስሐቅ በግ የእግዚአብሔር ልጅ የክርስቶስ ምሳሌ፥ ዕፀ ሳቤቅ የዕፀ መስቀል ምሳሌ መሆኑ ተጽፎአል (ዕብ. 11÷17፡18፤ ያዕ. 2÷21-23፤)፡፡ ዕፀ ሳቤቅ ማለትም ረጅም ሐረግ፥ የተመሳቀለና የተያያዘ ማለት እንደሆነ ምሁራኑ ይተረጉማሉ፡፡

### በትረ ሙሴና መስቀል፤

አምላከ ግፉዓን እግዚአብሔር ሕዝበ እስራኤልን አራት

መቶ ሠላሳ ዓመታት በመከራና በሰቆቃ ውስጥ ከኖሩ በኋላ መከራቸውን ተመልክቶ ነፃ እንዲወጡ ወስኖ፥ በሙሴ መሪነት ከምድረ ግብጽ ወጥተው ወደ ከነዓን ለመግባት በሚጓዙበት ጊዜ እጅግ አስፈሪና አስጨናቂ ወደ ሆነው ታላቁ ባሕረ ኤርትራ ሲደርሱ፥ ለመሻገር ቀርቶ ለማየትም የሚያስጨንቅ ስለሆነባቸው አለቀሱ፡፡ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ «በእጅህ ባለው በትር ባሕሩን ምታው፤ ትሻገራላችሁ» ብሎ ስለአዘዘው፥ ሙሴ በእጁ ባለው በትር ባሕሩ ሲመታው ባሕሩ ተከፍሎ ከስድት መቶ ሺህ በላይ የሆነ ሕዝበ በደረቅ ምድር ተሻግሯል፡፡

"...ነሥአ ሙሴ በትረ፥ ጸለየ፥ ወአማዕተበ፥ ውእቱኬ በአርአያ መስቀል" ሙሴ ባሕርን ከፍሎ ሕዝቡን ያሻገረበት በትር ኢየሱስ ክርስቶስ በበትረ መስቀሉ ባሕረ ኀጢአትን ከፍሎ የሰውን ልጆች ወደ ገነት መንግሥተ ሰማያት የማሻገሩ ምሳሌ ነውና፡፡ (ዘፀ. 14÷13፤ ቅዱስ ያሬድ)

### አርዌ ብርትና መስቀል፤

የያዕቆብ ልጆች ሕዝበ እስራኤል በሲና ምድረ በዳ እንደገና እግዚአብሔርን በመበደላቸው እግዚአብሔር ተቆጥቶ ነዘር የተባለ መርዛማ የበረሃ እባብን በላከባቸው ጊዜ ብዙ ሕዝብ አለቀ፡፡ የተረፈው ሕዝብ እግዚአብሔርን በድለናልና ሲሉ ወደ እግዚአብሔር በማልቀሳቸው፥ እግዘአብሔርም ሙሴን «አርዌ ብርትን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀለው፤ የተነደፈው ሁሉ የናሱን እባብ (አርዌ ብርት) ሲያይ በሕይወት ይኖራል» ብሎ ባዘዘው መሠረት ሙሴም የእባቡን ምሳሌ ሠርቶ ሰቀለው፡፡ ከተነደፉትም መርዙ ያልጸናባቸው ድምፁን ሰምተው፤ መርዙ የጸናባቸው መልኩን አይተው ድነዋል፡፡

የዚህንም ቀጥተኛ ምሳሌ ራሱ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው "ሙሴ እባብን በምድረ በዳ እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል፡፡" አርዌ ብርት የመስቀል ምሳሌ፥ ድምፁን ሰምተው መልኩን አይተው እንደዳኑ፥ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመስቀል ላይ በአሰማው የምሕረት ድምፅ፥ ባፈሰሰው ደመ መስቀሉ ለ5500 ዘመናት በሲኦል ጨለማ ውስጥ የነበሩ ነፍሳት ለመዳናቸው ምሳሌ ሆኖ ተጠቅሳ*ል፡፡ (ዮሐ. 3÷14-18፤ ራእ. 20÷2)

### የሙሴ እጅ አምሳለ መስቀል፤

አማሌቃውያን በራፌድ ሕዝበ እስራኤልን ሲዋጉ በተሰለፉ ጊዜ ሕዝቡ ፈርተው ስለተጨነቁ ሙሴ ሕዝቡን፦ «እኔ የእግዚአብሔርን በትር ይዤ በኮረብታው ላይ በእግዚአብሔር ፊት እቆማለሁ፤ እናንተ ሂዱና ተዋጉ» ብሎ በተራራው ላይ ሁለት እጆችን በአምሳለ መስቀል ሲዘረጋ ጠላቶቹ ድል እንደሆኑ፤ ጌታችን በዕለተ ዐርብ በመልዕልተ መስቀል ላይ ሁለት እጆቹን ዘርግቶ ተሰቅሎ አጋንንትን ድል በማድረግ ዓለምን አድኗልና፡፡ (ዘፀ. 17÷8፡9፤ ዘኍ. 21÷8፡9)

## ማጠቃለያ፤

የነገረ ቅዱስ መስቀል ታሪካዊ አመጣጥና ክብር ከዘባነ ኪሩቤል ጀምሮ በቀራንዮ የተደመደመ ሲሆን፤ ታሪኩ እጅግ ሰፊ በመሆኑ በዚህ ጽሑፍ ማጠቃለል ባይቻልም፥ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እንዳመሠጠሩት፦ አዳም የሞተበት በዕፀ በለስ ቢሆንም የዳነበትም በዕፀ መስቀል ነው፡፡ በመሆኑም በቅዱስ ዕፀ መስቀል የተገኘው ሕይወትና ትሩፋት፥ ጸጋና በረከት እጅግ ብዙ ሲሆን፤ ቅዱስ አትናቴዎስ፦ "ወአስተኃፈረ ኀጢአተ በዲበ ምድር፥ ወአብጠለ ሞተ በውስተ ሲኦል፥ ወሠዐረ መርገመ በዲበ ዕፀ መስቀል፤ወነሰተ ሙስና በውስተ መቃብር፤ የዓለም መድኀኒት ክርስቶስ በደመ መስቀሉ በምድር ላይ ኀጢአትን አሳፈረ፤ በሲኦል ሞትን አጠፋ፤ በመስቀል ላይ መርገምን ሻረ፤ በመቃብር ውስጥ ሙስና መቃብርን አጠፋ» (ሃይ.አበ.አትና. 30÷40) እንዳለ፤ ቅዱስ መስቀል የሕይወታችን መሠረት፥ የድል ምልክታችን፥ የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ በራችን፥ የዕርቅና የሰላም አርማችን መሆኑን አምነን እናከብረዋለን፡፡ (ዕብ. 13÷12፤ ሮሜ 5÷9፤ ኤፌ. 17)

**ቅዱስ እግዚአብሔር በኀይለ መስቀሉ ይባርከን፤ ይጠብቀን፡፡ አሜን፡፡**



# CALVARY

## IS THE NAME OF THE PLACE

September 26, 2025

EOTC Department of Public Relations

# Calvary is the name of the Place

Prepared by EOTC Department of Public Relations
and Approved by EOTC Scholars Council

**Editor in Chief**
Megabe selam Solomon Tolcha

**Deputy Editor**
M.H. Getabalaw Admasu

**Edition**
L.S. Nebiyu Eliyas

**Graphic Design**
Temesgen Tomas

**Translation**
M.S.Komos Abba Kaletsidk Mulugeta (Ph.D.)
Mhr. Akalewold Tessema (Ph.D.)
Mhr. Daniel Seifemichaiel

**Photography**
M.S. Abba Kiros Woldeab

**Publisher**
Tisaie Zegubaie Printing press

## Table of Content

Editorial ........................................................ 47
Message of H.H. The Patriarch ..................... 50
Message of H.G. The General Manager ......... 53
Message of Secretary General of the Holy Synod ........................................................... 56
Message of Deputy Manager of the Patriarchate for Spiritual Affairs ....................................... 59
Message of Deputy Manager of the Economic and Social Sector ......................................... 62
Calvary is the name of the Place .................. 64

© September 26, 2025
Addis Ababa, Ethiopia

# Editorial

## What Did Those Touched by the Love of the Cross Do?

The apostles, and all the holy ones who followed after the footsteps of the apostles - when they were touched by the love of the Cross, what did they do? And we, how should the love of the Cross touch us?

"And he who does not take his cross and follow after Me is not worthy of Me" (Matthew 10:38)

This powerful word is not only a call to those who are servants but it is expected to all who are saved in Christ to carry their own cross. Every servant or believer has a cross they are expected to carry daily. We must live our lives in such a way that reflects this daily cross-bearing. This is expressed by thinking about the love of the Cross and living accordingly.

We must consider the suffering of Christ's Cross as nailed into our minds. The place where the Lord was crucified, Golgotha, is the place of the skull. This signifies that the suffering of the Cross and the love of Christ should be embedded deep in our consciousness.

He was crucified to lift us from our fall for our redemption. The mystery of the Cross is complete redemption. When a person falls, to rise again, they must remember the Cross, visualize it with the eye of their mind and meditate upon it. As Scripture says of the Galatians, though they were deceived, Christ was presented before their very eyes as if crucified (Galatians 3:1). Likewise, when we are touched by the love of the Cross, we are freed from deception and sin, and constantly see Christ crucified for us in our hearts, with His love living in us. Those who are touched by the love of the Cross will carry the Cross.

**Carrying the Cross:** To carry the Cross means to constantly meditate on the suffering Christ endured to redeem humanity. When we are reminded of His suffering for our sake, we take up the Cross ourselves. Today, the suffering of the Cross doesn't only mean being stoned, cut by the sword, or burned alive like in the old times. Today's Crosses and tribulations are spiritual: victory over temptations like lust, impurity, idolatry, hatred, jealousy, anger, selfishness, drunkenness, division what St. Paul calls the works of the flesh (Galatians 5:19-21).

# Calvary is the name of the Place

Overcoming the works of the flesh through the power of the Cross is our modern-day way of carrying the Cross. When we are touched by the love of the Cross, we defeat the flesh and produce the fruit of the Spirit: love, joy, peace, patience, kindness, goodness, faithfulness, gentleness, self-control, and humility. When we are touched by the love of the Cross, we become doers of the golden rule, which the Lord spoke: "Do unto others as you would have them do unto you." (Matthew 7:12)

Whoever is touched by the love of the Cross obeys this word. The foundation of our faith is to love others. One who loves will not steal, kill, insult, or lie  because they love their neighbor and do not want harm to come to them. We obey the golden rule when we are filled with the love of the Cross. The Cross is a revelation of eternal love.

As we celebrate the Feast of the Cross today in our country and throughout the world, we must do so understanding the meaning of the Cross and being filled with its love. So, when we celebrate the Cross with fire, incense, drums, and singing in a land full of exile, conflict, division, quarrels, unrest, and the absence of peace  can we truly say we are filled with the love of the Cross? We must ask ourselves. When the love of the Cross touches us, we see Christ crucified in our hearts (Galatians 3:1). We overcome the works of the flesh and bear the fruit of the Spirit (Galatians 5:22).

Those touched by the love of the Cross truly see Christ  like Saint Stephen who, while being stoned, saw the heavens opened and Christ standing at the right hand of God. The love of the Cross reveals Christ's face even in suffering.

When we are touched by the love of the Cross: We achieve the goal of salvation. We look toward Paradise and the Kingdom of Heaven with hope. We find the true path of salvation, and more than all this we long to be with Christ. As Paul said: "I desire to depart and be with Christ..." (Philippians 1:20–23)

Indeed, we walk joyfully even through death because we are going to be with Christ. If we do not understand the meaning and love of the Cross, then our celebration of the Cross is not enough. We must be filled with it. This Feast of the Cross should be the only true answer and remedy to all the trials our country, church, and world face today.

This message is an excerpt from the 2018 edition of the Meskel (Feast of the Cross) magazine, prepared by the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church's Public Relations Department. It was written by senior scholars, edited by the department of scholars, and produced as a special message and teaching. The magazine is available both in print and on the Church's digital platforms.

We encourage everyone, in the love of God, to read and reflect on it and may God help us to

honor the love of the Cross not only in ceremony, but in our hearts.

**EOTC Public Relations Department**



# Calvary is the name of the Place

In the Name of the Father, and of the Son and of the Holy Spirit one God Amen!

## Message of His Holiness the Patriarch



*"He made peace in his cross, having put to death the enmity by it."*

*(Eph. 2:15:16)*

Before the crucifixion of Christ, the enmity that sin had caused was present between God and the creatures living on earth, especially between God and the human being who was the cause of sin; the enmity had separated God and man, both heavenly and earthly. To say that God and man were separated means that man was separated from God and from the glory and life that God had. This is the greatest punishment and the most dangerous death.

Since Adam and his children were the bearers of the punishment of sin, their mortality of bodies in this world was not enough. They were thrown into a place of punishment, rather than entering into the paradise of God's delight in Garden of Eden. Because a creature separated from God cannot enter the paradise of God's delight. This truth is explained by the contrast between the rich and the poor written in the Holy Gospel. (Luke 16:19-31)

In this state, man has lived separated from God for about five thousand five hundred years. during this long period of time, our God, did not leave man without hope. He comfort-

ed man by explaining his word of promise through the prophets in every age. The content of the promise was that God would save man through the redeeming blood of the Messiah.

When the time came for God to save the world, He sent his only begotten Son into the world. He took our flesh and our soul and became man; and he appeared in this world. This means that one of the three persons in Trinity, God the Son, was born from our Lady, the Holy Virgin Mary. He became incarnated, and became one body and one nature.

In this union, the Son of God, the Son of Mary, Jesus Christ, appeared in this world to save humanity through His redemptive death, and taught humanity the salvation of humanity. He made Godhood and the work of manhood one, without separation, omission, mixing, or change. In other words, by performing miracles that are impossible for creatures, He showed that He is both God and man; He taught humanity about the kingdom of God and the way of salvation.

Finally, for the salvation of the world, He was crucified on the cross and offered His redeeming blood as a sacrifice, saving us from death that came unto us as a result of our sin. With His shed blood, He carried our punishment and died in our place. Due to that, our debt to death was torn; The Garden of Eden was opened; and we were allowed to enter it. He proclaimed the great good news to all of us on the cross, “Today shalt thou be with me in paradise.” Therefore, glory be to our Lord Jesus Christ, who redeemed us with his shed blood; today, like the wise thief, we who pray in faith, saying, “Lord, remember me when thou come into thy kingdom,” are not awaited for hell, but for eternal peace.

We Christians celebrate the Feast of the Holy Cross with great religious ceremony because it has brought us out of hell and back to our former inheritance, to the Garden of Eden. That is why our father, Saint Yared, sang saying, “The cross is the above all things.” When we think of the Holy Cross, we primarily remember Christ, Christ’s love and salvation. We honor and venerate the Holy Cross, in remembering the Savior of the world Jesus Christ.

Just as honoring the flag of a country means honoring the people of that country; it is a truth and a reality that honoring the Holy Cross is honoring Jesus Christ. When we understand the Holy Cross in depth, its inner mystery clearly shows forgiveness, reconciliation, salvation, peace, unity, solidarity and forgiveness.

It is appropriate for us to honor, love and venerate the Holy Cross. However, it is not only to love, but also to show our love in order to receive the blessings of the Holy Cross. Let us remember that the love and honor we give to the Holy Cross is a direct love for God. The Lord Himself has said that love for God should be done with all our soul, with all our heart, with all our mind and with all our strength. If this is the truth, when we love the cross, it should be with determination to bring the

message of the cross into action. As we have learned in the Holy Scriptures, the message of the cross is to renounce sin and be reconciled; forgive one another; experience perfect peace among each other; be united and not divided; cooperate and not oppress and loving everyone.

So where is this all? This message of the cross, which gives us perfect peace, has been forgotten to the point that it seems to never concern us. We are not living according to the message of the cross, but the opposite. Although Christ has broken down the wall of division with the cross, many are saying, 'Hate is better for us' and are implementing conflict, division, oppression, murder, robbery, imprisonment, and rape in the form of a campaign. This is a very serious issue that is happening in our time. This type of choice cannot benefit us in any way except to harm and destroy us; we will never find a person or a country that benefited from violence.

Dear Ethiopians, my children in the Holy Spirit! Please, let us come to reconciliation and peace, to harmony and unity; our development and growth, our honor and glory, our strength and favor are in forgiveness and reconciliation. Doing so will never bring any harm or loss. It only needs discussing situations with openness and sincerity. All of you, our children, stop where you are and think; Look far and wide for your own and future generations' lasting benefit. We and future generations can benefit by accepting one Ethiopia as diverse, and the diverse Ethiopia as one.

We will prove this truth by peaceful discussion and listening, by giving time and thought to controversial issues, by being determined to answer all questions only through discussion and rule of law, and by providing opportunities for discussion, not by force and war. We must establish justice and equity; we must respect the existence of human life; we must ensure equality and unity; and to achieve this, we must accept fear of God as our common rule. When we do this, the message of the cross will become practical in our personal and community life.

Therefore, let us begin this New Year as the message of the cross, by killing hate with reconciliation, and by realizing the peace and unity of our people and our country. For this, we convey our fatherly message in the name of God to all Ethiopians, both at home and abroad, to show unremitting efforts through prayer, wisdom, and the sharing of good thoughts and advice.

Have a blessed feast of Holy Cross!

May our God bless and sanctify Ethiopia and its people!

Praise be to God; Amen.

**Abba Matthias I,**

Patriarch of Ethiopia Archbishop of Axum,
